# ሒሳብ

## የተማሪ መማሪያ መጽሐፍ

## 1ኛ ክፍል

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

ትምህርት ቢሮ

ISBN ቁጥር -

ዋጋ ብር -

ሀሳብ የተማሪ መማሪያ መጽሐፍ 1ኛ ክፍል

# ሒሳብ

## የተማሪ መማሪያ መጽሐፍ

## 1ኛ ክፍል




በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

ትምህርት ቢሮ

## የጥንቃቄ መልዕክት

### ተማሪዎች!

### ይህን የተማሪ መጽሐፍ በጥንቃቄ ያዙ!

ይህ መማሪያ መጽሐፍ በቀጣይ ዓመት የናንተ ወንድሞችና እህቶች የሚማሩበት የትምህርት ቤታችሁ ንብረት ነው! መጽሐፉ እንዳይበላሽ ወይም እንዳይጠፋ መጠንቀቅ አለባችሁ። መጽሐፉን በጥንቃቄ ለመያዝ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መመሪያዎች ተግባራዊ አድርጉ።

1. መጽሐፉን ከጉዳት ለመከላከል በላስቲክና በአሮጌ ጋዜጣ ወይም በካኪ ወረቀት ሸፍኑ።
2. መጽሐፉን ሁልጊዜ ደረቅና ንጹህ በሆነ ቦታ አስቀምጡት።
3. መጽሐፉን ለመጠቀም ስትዘጋጁ በቅድሚያ እጃችሁ እርጥበት የሌለውና ንጹህ መሆኑን አረጋግጡ።
4. በመጽሐፉ ሽፋን ወይም የውስጥ ገጾች ላይ አትጻፉ።
5. መጽሐፉን እያነበባችሁ እያላችሁ ንባባችሁን አቋርጣችሁ እንደገና ለማንበብ ስትፈልጉ ምልክት ማድረጊያ ብጣሽ ወረቀት ወይም ካርድ ተጠቀሙ።
6. በመጽሐፉ ውስጥ ያሉ ስእሎችን ወይም ገጾችን አትቅደዱ።
7. በመጽሐፉ ውስጥ የተቀደደ ወይም የተገነጠለ ገጽ ሲኖር በሙጫ ወይም በሌላ ንጹህ ማጣበቂያ ጠግኑት።
8. መጽሐፉን ከቦርሳችሁ ስታስገቡ ወይም ስታወጡ ጥንቃቄ አድርጉ።
9. መጽሐፉን ለሌላ ሰው ስታቀብሉም ሆነ ከሌላ ሰው ስትቀበሉ ተገቢውን ጥንቃቄ አድርጉ። ደህንነቱን አረጋግጣችሁ ተቀበሉ።
10. መጽሐፉን ለመጀመሪያ ጊዜ ስትቀበሉ ሽፋኖቹና ገጾቹ እንዳይገነጣጠሉ መጽሐፉን በጀርባው ጋደም አድርጋችሁ አስቀምጡት፤ ከዚያም ጥቂት ገጾችን ቀስ እያላችሁ በየተራ ግለጡ፤ በግራና በቀኝ እጃችሁ የያዛችሁትን የመጽሐፉን ክፍል በኃይል አትጫኑት (አትመንጭቁት)።

**ማሳሰቢያ፤** እነዚህ መመሪያዎች ሳይተገበሩ ቀርተው በመጽሐፉ ላይ አንዳች ጉዳት ከደረሰ በወጣው ሕግ መሠረት ተጠያቂ ያደርጋል።

# ሒሳብ

## የተማሪ መማሪያ መጽሐፍ

## 1ኛ ክፍል

**አዘጋጅ**

ብሬ ጌቴ

**አርታኢዎች**

ደረጀ ታየ

መንግስቱ ታየ

**ዲዛይነር**

ብሬ ጌቴ

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

ትምህርት ቢሮ

ይህ መጽሐፍ የተዘጋጀው በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በተመደበ በጀት በአብክመ ትምህርት ቢሮና በአማራ ምሁራን መማክርት ጉባዔ ትብብር ነው።

የመጽሐፉ ሕጋዊ የቅጂ ባለቤት © 2015 ዓ.ም. አብክመ ትምህርት ቢሮ ነው።

ምሁራን መማክርት ጉባዔ

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

ትምህርት ቢሮ

# ማውጫ


ገጽ

## ምዕራፍ 1 እስከ 20 ያሉ ቁጥሮች 1



ከ1 እስከ 5 ያሉ ቁጥሮችን መቁጠር ---- 2
ከ6 እስከ 9 ያሉ ቁጥሮችን መቁጠር ---- 4
ከ1 እስከ 5 ያሉ ቁጥሮችን ማንበብ እና መጻፍ ---- 6
ከ6 እስከ 9 ያሉ ቁጥሮችን ማንበብ እና መጻፍ ---- 12
ዜሮ ቁጥር ---- 17
ከ10 እስከ 15 ያሉ ቁጥሮች ---- 19
ከ16 እስከ 20 ያሉ ቁጥሮች ---- 21
የጨዋታ ጊዜ ---- 23
የምዕራፍ ማጠቃለያ መልመጃ ---- 24

## ምዕራፍ 2 እስከ 20 ያሉ ቁጥሮችን ማወዳደር 25




እስከ 10 ያሉ ቁጥሮችን በቅደም ተከተል ማስቀመጥ ---- 26
እስከ 10 ያሉ ቁጥሮችን ማወዳደር ---- 28
ከ11 እስከ 20 ያሉ ቁጥሮችን በቅደም ተከተል ማስቀመጥ 30
ከ11 እስከ 20 ያሉ ቁጥሮችን አወዳድሩ ---- 32
እስከ 10 ያሉ ቁጥሮችን ማጣመር እና መነጠል ---- 34
የጨዋታ ጊዜ ---- 38
የምዕራፍ ማጠቃለያ መልመጃ ---- 39

## ምዕራፍ 3 እስከ 10 ያሉ ቁጥሮችን መደመር 41




የመደመር ተረት ---- 42
የመደመር ዓረፍተ ነገር ---- 44
ዜሮን መደመር ---- 46

በመደመር 4ን፣ 5ን፣ እና 6ን ማግኘት 48
በመደመር 7ን ፣ 8ን እና 9ን ማግኘት 50
ቁልቁል መደመር 52
በማንኛውም ቅደም ተከተል መደመር 54
ወደፊት በመቁጠር መደመር 56
አስር በመሙላት መደመር 58
በእጥፍ በማስላት መደመር 60
የጨዋታ ጊዜ 62
የምዕራፍ ማጠቃለያ መልመጃ 63

## ምዕራፍ 4 እስከ 10 ያሉ ቁጥሮችን መቀነስ 65



የመቀነስ ተረቶች 66
የመቀነስ ዓረፍተ ነገር 68
ዜሮን እና ሁሉንም መቀነስ 70
ከ4፣ ከ5 እና ከ6 ላይ መቀነስ 72
ከ7 ፣ ከ8 ፣ ከ9 እና ከ10 ላይ መቀነስ 74
ቁልቁል መቀነስ 76
ወደኋላ በመቁጠር መቀነስ 77
የመደመር እና የመቀነስ ዝምድና 79
የጨዋታ ጊዜ 81
የምዕራፍ ማጠቃለያ መልመጃ 82

## ምዕራፍ 5 ጊዜ 85




የድርጊቶች ቅደም ተከተል 86
ጊዜ በሰዓት ሲገለጽ 88
ጊዜ በግማሽ ሰዓት ሲገለጽ 90
የሳምንቱ ቀናት 92
የጨዋታ ጊዜ 94
የምዕራፍ ማጠቃለያ መልመጃ 95

## ምዕራፍ 6 እስከ 100 ያሉ ቁጥሮች 97

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 |
| 11 | 12 | 13 | 14 | 15 | 16 | 17 | 18 | 19 | 20 |
| 21 | 22 | 23 | 24 | 25 | 26 | 27 | 28 | 29 | 30 |
| 31 | 32 | 33 | 34 | 35 | 36 | 37 | 38 | 39 | 40 |
| 41 | 42 | 43 | 44 | 45 | 46 | 47 | 48 | 49 | 50 |
| 51 | 52 | 53 | 54 | 55 | 56 | 57 | 58 | 59 | 60 |
| 61 | 62 | 63 | 64 | 65 | 66 | 67 | 68 | 69 | 70 |
| 71 | 72 | 73 | 74 | 75 | 76 | 77 | 78 | 79 | 80 |
| 81 | 82 | 83 | 84 | 85 | 86 | 87 | 88 | 89 | 90 |
| 91 | 92 | 93 | 94 | 95 | 96 | 97 | 98 | 99 | 100 |


በአስር መቁጠር 98

ቁጥሮችን በአስሮች መገመት 100

እስከ 100 ያሉ ቁጥሮችን በአንድ መቁጠር 102

እያለፉ መቁጠር 104

ቁጥሮችን በአስሮች እና በአንዶች መጻፍ 106

የቁጥር ቤት ዋጋ 108

እስከ 100 ያሉ ቁጥሮችን ማወዳደር 112

እስከ 100 ያሉ ቁጥሮችን በቅደም ተከተል ማስቀመጥ 115

የጨዋታ ጊዜ 117

የምዕራፍ ማጠቃለያ መልመጃ 118


## ምዕራፍ 7 ባለ ሁለት ሆሄ ቁጥሮችን መደመር እና መቀነስ 121







| | የ10 ቤት | የ1 ቤት |
|---|---|---|
| | 3 | 4 |
| + | 1 | 2 |
| | | 6 |

| | የ10 ቤት | የ1 ቤት |
|---|---|---|
| | 3 | 4 |
| + | 1 | 2 |
| | 4 | 6 |


አስሮችን መደመር እና መቀነስ 122

ከባለ ሁለት ሆሄ ቁጥር ጋር መደመር 124

ከባለ ሁለት ሆሄ ቁጥር ላይ መቀነስ 126

ባለ ሁለት ሆሄ ቁጥሮችን መደመር 128

ባለ ሁለት ሆሄ ቁጥሮችን መቀነስ 130

ድምሮችን እና ልዩነቶችን መገመት 132

የጨዋታ ጊዜ 134

የምዕራፍ ማጠቃለያ መልመጃ 135

## ምዕራፍ 8 የጂኦሜትሪ ምስሎች 137



ጥጥር ምስሎች 138
የጥጥር ምስል ገጾች 140
የጥጥር እና የጠለል ምስሎች ዝምድና 142
የጠለል ምስሎች ጎኖች እና መለያያዎች 144
የጨዋታ ጊዜ 146
የምዕራፍ ማጠቃለያ መልመጃ 147

## ምዕራፍ 9 ልኬት 149



ርዝመትን ማወዳደር 150
መደበኛ ያልሆኑ የርዝመት መለኪያዎች 152
ክብደትን ማወዳደር 154
መደበኛ ያልሆኑ የክብደት መለኪያዎች 156
ይዘትን ማወዳደር 158
መደበኛ ያልሆኑ የይዘት መለኪያዎች 160
የጨዋታ ጊዜ 162
የምዕራፍ ማጠቃለያ መልመጃ 163

## ምዕራፍ 10 የኢትዮጵያ ገንዘብ 165



የኢትዮጵያ ሳንቲሞች 166
የገንዘብ መጠንን መቁጠር 168
የጨዋታ ጊዜ 170
የምዕራፍ ማጠቃለያ መልመጃ 171

# መግቢያ

## ሥርዓተ ትምህርቱን ማዘጋጀት ለምን አስፈለገ?

ከሥርዓተ-ትምህርቱ ጋር የተያያዙ ችግሮችን ለመፍታት የተለያዩ ጥናት እና ምርምሮች ተካሂደዋል። ከእነዚህም አንዱ በሀገር አቀፍ ደረጃ በስፋት የተካሄደው የትምህርትና ሥልጠና ፍኖተ-ካርታ ጥናት ዋናው ነው። ይህ እና ሌሎችም ተመሳሳይ ርእሶች ዙሪያ የተካሄዱት ጥናትና ምርምሮች ሥርዓተ ትምህርቱ በይዘት የታጨቀ፣ በትምህርት አይነቶች ብዛት የተወጠረ፣ በአብዛኛው ይዘት ማስታዎስን ትኩረት ያደረገ፣ ከተማሪዎችና ከማህበረሰቡ ህይወትና ኑሮ፣ ምርታማነት እንዲሁም ከሀገር በቀል እውቀት ጋር ያልተቆራኘ፣ ተማሪዎች ተገቢውን ግብረገባዊ እውቀትና ክህሎት እንዲላበሱ ያላደረገ፣ በቴክኖሎጂ ያልተደገፈ እና ልዩ ፍላጎትና ልዩ ተሰጥኦ ያላቸውን ተማሪዎች በተገቢው መንገድ ከማስተናግድ አኳያ ክፍተት ያለበት መሆኑ ተመላክቷል። በተጨማሪም ስርዓተ ትምህርቱ የ21ኛው ክፍለ ዘመን የሚጠይቀውን እውቀትና ክህሎት ማለትም ለመማር መማርን፣ በጥልቀት ማሰብና ችግር ፈችነትን፣ የፈጠራ አስተሳሰብና አዳዲስ ግኝቶች ማፍለቅን፣ ተግባቦትን፣ ትብብርን፣ መሪነትና ውሳኔ ሰጭነትን፣ የቴክኖሎጂ እውቀትን እና የባህል ማንነትና አለማቀፋዊ ዜግነትን ማስጨበጥ የማይችል መሆኑን በማመላከት የሥርዓተ-ትምህርት መሻሻል እና ለውጥ እንዲካሄድ የሚያመላክቱ ምክረ-ሃሳቦችን ሰንዝረዋል።

ይህንን መነሻ በማድረግም ሰፊ የውይይት እና የምክክር መድረኮች ተዘጋጅተው ህብረተሰቡ እንዲወያይ በማድረገ የለውጥ መርሃ ግብሮች ተቀርፀው ወደ ትግበራ ተገብቷል። ከእነዚህ የለውጥ መርሃ ግብሮች ውስጥ አንዱ አዲስ የአጠቃላይ ትምህርት ሥርዓተ-ትምህርት መቅረጽ ሲሆን ቀደም ሲል የነበሩትን ችግሮች ለመቅረፍ በሚያስችል መልኩ የሥርዓተ-ትምህርት ለውጥ ዝግጅት ተድርጓል።

በዚህም መሠረት አዲሱን የአጠቃላይ ትምህርት ሥርዓተ-ትምህርት ተግባራዊ ለማድረግ እንዲቻል በመጀመሪያ ለመማሪያ ማስተማሪያ መጻሕፍት ዝግጅት የሚያግዙ ሰነዶች ማለትም የተማሪው የባህሪ ገጽታ፣ የሥርዓተ-ትምህርት ማዕቀፍ፣ የይዘት ፍሰት፣ ተፈላጊ የመማር ብቃት እና መርሃ-ትምህርቶች እንደ ሀገር ተዘጋጅተዋል። በእነዚህ ሰነዶች መነሻነትም በክልላችን የመጀመሪያ ደረጃ(ከ1ኛ-6ኛ) እና የመካከለኛ ደረጃ(7ኛና 8ኛ) ክፍሎች የየትምህርት አይነቶች የተማሪዎች መማሪያ እና የመምህራን ማስተማሪያ መጽሐፍት ተዘጋጅተዋል።

## የመጽሐፍት አተገባበር

መጽሐፉ ተማሪዎች ከዚህ ቀደም ከሚያውቁትና ከአካባቢያቸው ይዘውት ከሚመጡት ተሞክሮና እውቀት በመነሳት ተግባር ተኮር እና አሳታፊ በሆነ መልኩ እንዲማሩ ሆኖ ስለተዘጋጀ ተማሪዎች ትምህርቱን በጥልቀት ይገነዘቡታል ወይም ይረዱታል ተብሎ ይታመናል፡፡ ተማሪዎችና መምህራን አካባቢያቸውን እና ያካበቱትን ዕውቀትና ተሞክሮ መሰረት በማድረግ በመጽሐፉ ውስጥ የተካተቱ የተለያዩ ተግባራትን በአግባቡ በመተግበር ተማሪዎቻችን ይዘቶችን መማር ብቻ ሳይሆን የመማር ክህሎታቸውን እንዲያሳድጉ ይጠበቃል፡፡ በመሆኑም መምህራን ለይዘቱ ተስማሚ ተብለው የተጠቆሙ የማስተማሪያ እና መማሪያ ዘዴዎችን በአግባቡ በመተግበርና ሌሎች ተገቢ ዘዴዎችን ተጨባጭ ሁኔታንና የተማሪዎችን አቅምና ፍላጎት መሰረት አድርጎ በመምረጥ ተማሪተኮር/አሳታፊ አድርገው የመማር ማስተማሩን ተግባር መፈጸም የሚጠበቅባቸው ሲሆን ተማሪዎች ደግሞ በትምህርቱ ክፍለ ጊዜ መጽሐፍቱን ከእጃቸው ሳይለዩ ትምህርቱን መከታተል ይኖርባቸዋል፡፡

## ውድ ተማሪዎቻችን!

መጽሐፉን በጥንቃቄ በመያዝ በአግባቡ መጠቀም አለባችሁ፡፡ በማንኛውም አገርና ሁኔታ መማር የትውልድን የወደፊት ሁኔታ ይወስናል፡፡ መማር ለማንኛውም ማህበራዊ፣ ሰብዓዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት መሰረት ነው፡፡ በመጽሐፉ ውስጥ ያሉትን ሁሉንም ተግባራት፣ ይዘቶችና ጥያቄዎች በአግባቡ በመስራትና በማጥናት ጥልቀት ያለው ክህሎትን እና ግንዛቤን ማዳበር ይገባችኋል፡፡

## ውድ ወላጆች/አሳዳጊዎች!

የተማሪዎችን መማር የተሳለጠ ለማድረግ የመማሪያ መጻሕፍት ያላቸው ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው፡፡ ስለሆነም ተማሪዎች መጽሐፉን በጥንቃቄ ይዘው እንዲጠቀሙ ማድረግ ይኖርባችኋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ተማሪዎች መጽሐፉን ት/ቤት ይዘው እንዲሄዱ ማበረታታት፣ ከመምህሮቻቸው የሚሰጡ ተግባራትን በትክክል እንዲፈጽሙና እንዲያጠኑ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣ ትምህርት ቤት በመሄድ ከመምህራን ጋር በመገናኘት ስለ ልጅዎ የመማር ዕውቀትና የባህሪ ለውጥ በመጠየቅ ክፍተቱን በመለየት ምክር በመሥጠት ማስተካከል ይጠበቅባችኋል፡፡ በመሆኑም ትምህርት የሁሉም ነገር መሰረት መሆኑን በመገንዘብ መማርን ከመንግስት ስራ መያዝ ጋር ብቻ ሳታቆራኙት/ሳያያይዙት ልጆችን ሁልጊዜ ወደ ትምህርት ቤት መላክ አለባችሁ፡፡

# ምዕራፍ 1 እስከ 20 ያሉ ቁጥሮች



**የመግቢያ ጥያቄ**

ስንት ተማሪዎችን ተመለከታችሁ? የቆሙ ተማሪዎች ስንት ናቸው? የተቀመጡትስ?

## የቀደመ እውቀታችሁን ከልሱ

1. እነዚህን ምስሎች ሳሉ፡፡



2. ይህን ○ ምስል በዚህ  ተጠቅማችሁ ቀቡ፡፡
3. ይህን □ ምስል በዚህ  ተጠቅማችሁ ቀቡ፡፡
4. ይህን △ ምስል በዚህ  ተጠቅማችሁ ቀቡ፡፡
5. ሦስት ሙዝ የያዘው እቃ የቱ ነው?



# ከ1 እስከ 5 ያሉ ቁጥሮችን መቁጠር

**የመማር ውጤቶች**

- ከ1 እስከ 5 የሚደርሱ ነገሮችን መቁጠር፡፡

**ዋና ቃላት**

- ቁጥር
- መቁጠር

ስንት እህት አላችሁ? ስንት ወንድም አላችሁ?

የአንድ እጃችሁን ጣቶች መቁጠር ትችላላችሁን?

የሚከተሉትን መዝሙሮች ዘምሩ፡፡

**ምሳሌ**

ከመምህራችሁ ጋር ዘምሩ፡፡

| | |
|---|---|
| **አንድ አንድ አንድ**<br>መማር የሚወድ<br>**አንድ** ተማሪ<br>ሲያነብ በባትሪ |  |
|  | **ሁለት ሁለት ሁለት**<br>ከትምህርት ቤት<br>**ሁለት** ህጻናት<br>ሄዱ ወደ ቤት |
| **ሦስት ሦስት ሦስት**<br>ዛሬ ማህሌት<br>**ሦስት** እርግቦች<br>ሲበሩ አየች |  |

## መልመጃ

ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር ዘምሩ፡፡



አራት አራት አራት

ዝንጀሮ ትናንት

አራት ብርቱካን

በላ ብቻውን

አምስት አምስት አምስት

አምስት ጥንቸሎች

ወጡ ተራራ

ሊወዳደሩ ከኤሊ ጋራ



## ፕሮብሌም መፍታት

በጎች ስንት ናቸው?

ጫጩቶች ስንት ናቸው?

የትኞቹ ይበዛሉ?

እንዴት መቁጠር እንደቻላችሁ አብራሩ፡፡



**ሒሳብን በቤት:** ልጆችዎ ከ1 እስከ 5 የሚደርሱ በቤት ውስጥ የሚገኙ ነገሮችን እንዲቆጥሩ ያድርጉ፡፡

## ከ6 እስከ 9 ያሉ ቁጥሮችን መቁጠር

**የመማር ውጤቶች**
- ከ6 እስከ 9 የሚደርሱ ነገሮችን መቁጠር፡፡

ስንት የቤተሰብ አባላት አላችሁ?

የደብተራችሁን ብዛት መቁጠር ትችላላችሁን?

**ቁጥር** ስንት ነገሮች እንዳሉ ይገልጻል፡፡

ምሳሌውን ተመልከቱ፡፡

### ምሳሌ

ከመምህራችሁ ጋር ዘምሩ፡፡

ስድስት ስድስት ስድስት
ስድስት ድመቶች ሆነው
በጋራ ወተት ጠጥተው
ይጫዎታሉ ተደስተው





ሰባት ሰባት ሰባት
ሰባት ቢጫ ቢራቢሮዎች
ሲደንሱ ከአበባዎች
ደስ ይላሉ ለልጆች

ቦኖዎችን 🔴🟡 በመጠቀም ቁጠሩ፡፡

ዝንጀሮዎች ስንት ናቸው? አልጋው ላይ ከተኙት እና መሬት ላይ ከወደቁት የትኞቹ ይበዛሉ? እንዴት አወቃችሁ?



## መልመጃ

ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር ዘምሩ።

| | |
|---|---|
| ስምንት ስምንት ስምንት<br>ስምንት ታታሪ ጉንዳኖችን<br>ተሸክመው ቅጠሎችን<br>ሲሄዱ አየሁ በደጅአችን |  |

| | |
|---|---|
|  | ዘጠኝ ዘጠኝ ዘጠኝ<br>ዘጠኝ ብዮችን ዛሬ<br>ከጓደኛየ ተበድሬ<br>ተጫወትኩኝ ከሰፈሬ |

## ፕሮብሌም መፍታት



ቦኖዎችን  በመጠቀም ቁጠሩ።

ጥጃዎች ስንት ናቸው?

የበግ ግልገሎች ስንት ናቸው?

ከግልገሎች እና ከጥጃዎች የትኞቹ ይበዛሉ? እንዴት አወቃችሁ?

**ሒሳብን በቤት:** ልጆችዎ ከ6 እስከ 9 የሚደርሱ በቤት ውስጥ የሚገኙ ነገሮችን እንዲቆጥሩ ያድርጉ።

# ከ1 እስከ 5 ያሉ ቁጥሮችን ማንበብ እና መጻፍ

ከ1 እስከ 5 ያሉ ቁጥሮችን ማንበብ እና መጻፍ እንድትችሉ የሚከተለውን ምሳሌ ተመልከቱ:: ቁጠሩ:: ቁጥሮችን አንብቡ:: ቁጥሮችን ጻፉ::

**የመማር ውጤቶች**

- ከ1 እስከ 5 የሚደርሱ ነገሮችን መቁጠር::
- ከ1 እስከ 5 ያሉ ቁጥሮችን ማንበብ እና መጻፍ::

**ምሳሌ**


















| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | |
| | | | | | | |






  2

  2

  2

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 2 | | | | | | |
| | | | | | | |









| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 3 | | | | | | |
| | | | | | | |






4



4



4

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 4 | | | | | | |
| | | | | | | |








5



5



5

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 5 | | | | | | |
| | | | | | | |

## መልመጃ

**አስተውሉ**
ቁጥር ስንት ነገሮች እንዳሉ ይገልጻል::

ይኸን በመሳል ቁጥሩን አሳዩ::

1. 
4

2. 3

ይኸን በመጠቀም ቁጥሩን አሳዩ::

3. 2

4. 5

ስንት ናቸው? ቁጥሩን ፃፉ::

5. 
2 ሁለት

6. 
______ ሦስት

7. 
______ አንድ

8. 
______ አምስት

9. 
______ አራት

10. 
______ ሦስት

## ፕሮብሌም መፍታት

5ን የሚገልጹ ነገሮችን ለዩ::



**ሒሳብን በቤት:** ከ1 እስከ 5 ያለ ቁጥር ይናገሩ:: ልጆችዎ ቁጥሩን በስዕል ይግለጹ:: ቁጥሩንም ይጻፉ:: ከ1 እስከ 5 የሚደርሱ ነገሮችን (ምሳሌ ጠጠር: ባቄላ) እንዲቆጥሩ ያድርጉ::

## ከ6 እስከ 9 ያሉ ቁጥሮችን ማንበብ እና መጻፍ

**የመማር ውጤቶች**

- ከ6 እስከ 9 የሚደርሱ ነገሮችን መቁጠር።
- ከ6 እስከ 9 ያሉ ቁጥሮችን ማንበብ እና መጻፍ።

ከ6 እስከ 9 ያሉ ቁጥሮችን ለማንበብ እና ለመጻፍ የሚከተለውን ምሳሌ ተመልከቱ።

**ምሳሌ**

በምስሉ ላይ ያሉ ነገሮችን ቁጠሩ። ቁጥሮችን አንብቡ። ቁጥሮችን ጻፉ።








6



6



6

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 6 | | | | | | |
| | | | | | | |





ሰባት



7



7



7

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 7 | | | | | | |
| | | | | | | |








8



8



8

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 8 | | | | | | |
| | | | | | | |








9



9



9

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 9 | | | | | | |
| | | | | | | |

## መልመጃ

በደብተራችሁ ላይ ይኸን ◯ በመሳል ቁጥሩን አሳዩ።

1. 6 ◯ ◯ ◯ ◯ ◯ ◯

2. 7

ይህን ወይንም በመጠቀም ቁጥሩን አሳዩ።

3. 9

4. 8

ቁጠሩ። ቁጥሩን በደብተራችሁ ጻፉ።

5.  6 ስድስት

6.  ______ ስምንት

7.  ______ ዘጠኝ

8.  ______ ሰባት

9.  ______ ስምንት

10.  ______ ስድስት

## ፕሮብሌም መፍታት



9ን የሚገልጹ ነገሮችን ለዩ።

    

**ሒሳብን በቤት:** ከ6 እስከ 9 ያለ አንድ ቁጥር ይናገሩ።ልጆችዎ ቁጥሩን በስዕል ይግለጹ። ቁጥሩንም ይጻፉ። ከ6 እስከ 9 የሚደርሱ ነገሮችን (ለምሳሌ ጠጠር) እንዲቆጥሩ ያድርጉ።

# ዜሮ ቁጥር

**የመማር ውጤቶች**

- ዜሮ ቁጥርን ማንበብ እና መጻፍ።

**ዋና ቃል**

- ዜሮ

ዜሮ ምንድን ነው? ስንት ነገሮችን ይወክላል?

የሚከተለውን ተመልከቱ።

**ምሳሌ**

**አምስት** ጣፋጭ ብርቱካን ከቅርጫቱ ውስጥ ይታያል።
አንዱን ብትመገቡ
ስንት ብርቱካን ይቀራል?





**አራት** ጣፋጭ ብርቱካን ከቅርጫቱ ውስጥ ይገኛል።
አንዱን ብትመገቡ
ስንት ብርቱካን ይቀራል?





**ሦስት** ጣፋጭ ብርቱካን ከቅርጫቱ ውስጥ ይገኛል።
አንዱን ብትመገቡ
ስንት ብርቱካን ይቀራል?





**ሁለት** ጣፋጭ ብርቱካን ከቅርጫቱ ውስጥ ይገኛል።
አንዱን ብትመገቡ
ስንት ብርቱካን ይቀራል?





**አንድ** ጣፋጭ ብርቱካን ከቅርጫቱ ውስጥ ይገኛል።
አንዱን ብትመገቡ
ስንት ብርቱካን ይቀራል?





**ዜሮ**



## መልመጃ

ከዛፉ ቅርንጫፍ ላይ ያሉትን ወፎች ቁጠሩ። ቁጥሩን ጻፉ።













## ፕሮብሌም መፍታት

1. አንዳንድ የብርቱካን ዝርያዎች ዘር የላቸውም።

በምስሉ ላይ ስንት የብርቱካን ዘሮችን ተመለከታችሁ?



2. 0ን የሚገልጹ ነገሮችን ለዩ።



**ሒሳብን በቤት:** 0ን ሊወክል የሚችል ነገር ለልጆችዎ ይስጡ። ልጆችዎ ቁጥሩን እንዲጽፉ ያድርጉ።

# ከ10 እስከ 15 ያሉ ቁጥሮች

**የመማር ውጤቶች**

- ከ10 እስከ 15 የሚደርሱ ነገሮችን መቁጠር፣ ማንበብ እና መፃፍ፡፡

ከ10 እስከ 15 ያሉ ቁጥሮችን እንዴት መግለጽ ይቻላል?

የሚከተለውን ተመልከቱ፡፡

| ተመልከቱ | ወክሉ | ስያሜውን አንብቡ | ቁጥሩን አስተውሉ |
|---|---|---|---|
|  |  | አስር | 10 |
|  |  | አስራ አንድ | 11 |
|  |  | አስራ ሁለት | 12 |
|  |  | አስራ ሦስት | 13 |
|  |  | አስራ አራት | 14 |
|  |  | አስራ አምስት | 15 |

**ምሳሌ**

ቦኖ  እና ሰንጠረዥ በመጠቀም ቁጥሮችን ግለጹ፡፡

1. 11



2. 14



ቁጠሩ:: ቁጥሩን በደብተራችሁ ላይ ጻፉ::

3. 

_______ አስር

4. 

_______ አስራ አምስት

5. ከ10 እስከ 15 ያሉ ቁጥሮች የሚያመሳስላቸው ምንድን ነው? ተወያዩ::

## መልመጃ

ቦኖ  እና ሰንጠረዥ በመጠቀም ቁጥሮችን ግለጹ::

1. **12** 

2. **15** 

ቁጠሩ:: ቁጥሩን በደብተራችሁ ላይ ጻፉ::

3. 

_______ አስራ ሦስት

4. 

_______ አስራ አንድ

5. 

_______ አስራ አራት

6. 

_______ አስራ ሁለት

## ፕሮብሌም መፍታት

15ን የሚገልጹ ነገሮችን ለዩ::



**ሒሳብን በቤት:** ከ10 እስከ 15 ያለ አንድ ቁጥር ይናገሩ:: ልጆችዎ የዚያን ቁጥር ያክል ስዕል እንዲስሉ እና ቁጥሩንም እንዲጽፉ ያድርጉ::

# ከ16 እስከ 20 ያሉ ቁጥሮች

**የመማር ውጤቶች**

- ከ16 እስከ 20 የሚደርሱ ነገሮችን መቁጠር፣ ማንበብ እና መጻፍ፡፡

ከ16 እስከ 20 ያሉ ቁጥሮችን እንዴት መግለጽ ይቻላል?

የሚከተለውን ተመልከቱ፡፡

| ተመልከቱ | በአስር ማዕቀፍ ወክሉ | ስያሜውን አንብቡ | ቁጥሩን አስተውሉ |
|---|---|---|---|
|  |  | አስራ ስድስት | 16 |
|  |  | አስራ ሰባት | 17 |
|  |  | አስራ ስምንት | 18 |
|  |  | አስራ ዘጠኝ | 19 |
|  |  | ሃያ | 20 |

## ምሳሌ

ቦኖ እና ሰንጠረዥ በመጠቀም ቁጥሮችን አሳዩ፡፡

1. 18



2. 19



ቁጠሩ። ቁጥሩን በደብተራችሁ ላይ ጻፉ።

3. 

______ አስራ ሰባት

4. 

______ ሃያ

5. 2 እና 20 እንዴት ነው የሚለያዩት? ተወያዩ።

## መልመጃ

ቦኖ  እና ሰንጠረዥ በመጠቀም ቁጥሮችን አሳዩ።

1. 16

2. 20

ቁጠሩ። ቁጥሩን በደብተራችሁ ላይ ጻፉ።

3. 

______ አስራ ስምንት

4. 

______ አስራ ስድስት

## ፕሮብሌም መፍታት

በአጠቃላይ ስንት አበባዎች አሉ?

ቁጥሩን ጻፉ። የማን አበባዎች ይበዛሉ?



የአበበች አበባዎች



የአበበ አበባዎች

**ሒሳብን በቤት:** ከ16 እስከ 20 ያለ አንድ ቁጥር ይናገሩ። ልጆችዎ የዚያን ቁጥር ያክል ምስሎችን በመጠቀም ቁጥሩን እንዲወክሉ እና ቁጥሩንም እንዲጽፉ ያድርጉ።

# የጨዋታ ጊዜ

## የመቁጠር ጨዋታ




**አስፈላጊ ቁሶች:** 1 ዳይ ፣ 2 ቦኖዎች ወይም ሌላ መቁጠሪያዎች

**የጨዋታው ህግ:** ጨዋታን ለመጀመር ቦኖአችሁን ከ**መነሻ** ላይ አስቀምጡ።በተራ ዳይ ወርውሩ። ከዚያም የወጣውን ቁጥር ያክል በቅጠሎቹ ላይ እየዘለላችሁ ተጓዙ። በዘለላችሁበት ቦታ ሁሉ ያሉ ቁጥሮችን ተናገሩ። ከዚያም ቦኖአችሁን አስቀምጡ። በቀጣይ ዙር ዳይ ስትወረውሩ አሁን ከአላችሁበት ቦታ መቁጠር ቀጥሉ። አሸናፊ ለመሆን በቅድሚያ ቢራቢሮዋ ላይ መድረስ ነው።

# የምዕራፍ ማጠቃለያ መልመጃ

ስንት ናቸው? ቁጥሩን በደብተራችሁ ጻፉ፡፡

1. 

_______ ሦስት

2. 

_______ አምስት

3. 

_______ አስራ ሦስት

4. 

_______ አስራ ስድስት

ቁጠሩ፡፡ ቁጥሩን በደብተራችሁ ጻፉ፡፡

5.  _______

6.  _______

7.  _______

8.  _______

9.  _______

10.  _______

11. 10ን የሚገልጹ ነገሮችን ለዩ፡፡



# ምዕራፍ 2 እስከ 20 ያሉ ቁጥሮችን ማወዳደር



**የመግቢያ ጥያቄ**
ስንት ቢራቢሮዎችን ተመለከታችሁ? ከአበባዎች ቁጥርና ከቢራቢሮዎች ቁጥር የቱ ይበልጣል?

## የቀደመ እውቀታችሁን ከልሱ

1. ቁጥሮችን ከተሰጡት ምስሎች ጋር አዛምዱ::



1 2 3 4 5

ስንት ናቸው:: ቁጥሩን ጻፉ::

2. 

3. 

4. በቁጥር የትኞቹ ይበልጣሉ?



5. የትኛው ፍራፍሬ በቁጥር ያንሳል?



# እስከ 10 ያሉ ቁጥሮችን በቅደም ተከተል ማስቀመጥ

**የመማር ውጤቶች**
- እስከ 10 ያሉ ቁጥሮችን በቅደም ተከተል ማስቀመጥ::

**ዋና ቃላት**
- የቁጥር መስመር
- በፊት፣ በኋላ፣ መካከል

የቁጥር መስመር ቁጥሮችን በቅደም ተከተል ያሳያል::




6 ከ7 ቀድሞ ይገኛል:: ማለትም 6 ከ7 **በፊት** ይገኛል::

8 ከ7 ተከትሎ ይገኛል:: ማለትም 8 ከ7 **በኋላ** ይገኛል::

7 ደግሞ በ6 እና በ8 **መካከል** ይገኛል::

6 ከ7 በ1 ያንሳል::
8 ደግሞ ከ7 በ1 ይበልጣል::

## ምሳሌ




1. ከ8 **በፊት** የሚገኘውን ቁጥር በደብተራችሁ ላይ ጻፉ:: 7

**አስተውሉ**
መጀመሪያ 8ን ከቁጥር መስመሩ ላይ ፈልጉ:: ከዚያም ከ8 ቀድሞ የሚገኘውን ቁጥር ውሰዱ::

2. በ 8 እና በ10 **መካከል** የሚገኘውን ቁጥር ጻፉ::

ክፍት ቦታውን የሚያሟላውን ቁጥር ለዩ::

| 3. **በፊት** | 4. **መካከል** | 5. **በፊት** እና **በኋላ** |
|---|---|---|
| ____ ፣ 4 ፣ 5 | 0 ፣ ____ ፣ 2 | ____ ፣ 3 ፣ ____ |
| ____ ፣ 1 ፣ 2 | 6 ፣ ____ ፣ 7 | ____ ፣ 9 ፣ ____ |

6.



7.



8.



9. ከአንድ ቁጥር በፊት እና በኋላ የሚመጡ ቁጥሮች የሚለያዩት እንዴት ነው? ተወያዩ::

## መልመጃ

0 1 2 3 4 5 6 7 8 9 10

ክፍት ቦታውን የሚያሟላውን ቁጥር ለዩ፡፡

**1. በኋላ**

0 ፣ 1 ፣ ____

3 ፣ 4 ፣ ____

**2. በፊት**

____ ፣ 8 ፣ 9

____ ፣ 6 ፣ 7

**3. በፊት እና በኋላ**

____ ፣ 1 ፣ ____

____ ፣ 8 ፣ ____



4. 7 8 ☐

5. ☐ 4 ☐

6. 1 ☐ 3

## ፕሮብሌም መፍታት

ምስሎችን በመጠቀም ፕሮብሌሙን ፍቱ፡፡

1. በክፍል ውስጥ ካሳ ከዘሪሁን በኋላ ተቀምጧል፡፡ ጀማል ደግሞ ከካሳ በኋላ ተቀምጧል፡፡ መካከል ላይ የተቀመጠው ማን ነው? __________

2. ሃይማኖት 9 ብዮች አሏት፡፡ ሠዓዳ ደግሞ ከሃይማኖት በ1 ያነሰ ብይ አሏት፡፡ የሠዓዳ ብዮች ስንት ናቸው? ሠዓዳ _____ ብዮች አሏት፡፡

3. ሰይድ 7 ዓመቱ ነው፡፡ ብርሃኑ እና ሐያት 2 የሰፈር ጓደኞቹ ናቸው፡፡ የብርሃኑ እድሜ ከሰይድ በ2 ዓመት ያነሰ ነው፡፡ የሐያት እድሜ ደግሞ ከሰይድ በ2 ዓመት የበለጠ ነው፡፡ የብርሃኑ እና የሐያት እድሜ ስንት ነው?

**ሒሳብን በቤት:** ከ1 እስከ 10 ካሉ ቁጥሮች መካከል አንዱን ቁጥር በመስጠት ልጆችዎ ከተሰጠው ቁጥር በፊት እና በኋላ የሚመጡ ቁጥሮችን እንዲለዩ ይጠይቁ፡፡

# እስከ 10 ያሉ ቁጥሮችን ማወዳደር

**የመማር ውጤቶች**

- ምስሎችን እና ቃላትን በመጠቀም እስከ 10 ያሉ ቁጥሮችን ማወዳደር።

**ዋና ቃላት**

- ያንሳል
- ይበልጣል
- እኩል ይሆናል

ሁለት ቁጥሮችን እንዴት ማወዳደር እንደሚቻል ታውቃላችሁን? የሚከተለውን ተመልከቱ።



7 **ያንሳል** ከ9



9 **ይበልጣል** ከ8 7 **እኩል ይሆናል** ከ7

## ምሳሌ

ቁጠሩ። ቁጥሩን በደብተራችሁ ጻፉ። ብዙ አባል ያለውን ቡድን ለዩ።

1\.



2\.



ቁጥሮችን ከአወዳደራችሁ በኋላ ትክክለኛ የሆነውን አገላለጽ ለዩ።

3\.

 5

 6

5 ይበልጣል ከ6 5 ያንሳል ከ6 5 እኩል ይሆናል ከ6

**አስተውሉ**
5 ነገሮች ከ6 ነገሮች ያንሳሉ።

4\.

4 3



4 ይበልጣል ከ3 4 ያንሳል ከ3

4 እኩል ይሆናል ከ3

5\.

6 6



6 ይበልጣል ከ6 6 ያንሳል ከ6

6 እኩል ይሆናል ከ6

6\. 5 ______ 4

ይበልጣል ያንሳል እኩል ይሆናል

7\. 1 ______ 3

ይበልጣል ያንሳል እኩል ይሆናል

## መልመጃ

ቁጠሩ፡፡ ቁጥሩን በደብተራችሁ ጻፉ፡፡ ብዙ አባል ያለውን ቡድን ለዩ፡፡

1. 

2. 

እውነት የሆነውን አገላለጽ ለዩ፡፡

3. 
10 ይበልጣል ያንሳል 10
እኩል ይሆናል

4. 
8 ይበልጣል ያንሳል 7
እኩል ይሆናል

5. 
8 ____ 9
ይበልጣል ያንሳል እኩል ይሆናል

ቁጥሮችን ከአወዳደራችሁ በኋላ ትክክለኛ የሆነውን መልስ ምረጡ፡፡

6. 8 _______ 6
ይበልጣል ያንሳል
እኩል ይሆናል

7. 0 _______ 1
ይበልጣል ያንሳል
እኩል ይሆናል

8. 7 _______ 7
ይበልጣል ያንሳል
እኩል ይሆናል

## ፕሮብሌም መፍታት

1. በስዕል ወረቀት ላይ 8 አረንጓዴ የሎሚ ምስል ሳሉ፡፡ ከዚያም 6 ቢጫ የሎሚ ምስል ሳሉ፡፡ ትንሽ አባል ያለውን ምስል አክብቡ፡፡

2. አልማዝ 7 ኳሶች አሏት፡፡ ሶልያና 5 ኳሶች አሏት፡፡ ሐሊማ ደግሞ 9 ኳሶች አሏት፡፡ ብዙ ኳሶች ያሏት ማን ናት? ጥቂት ኳሶች ያሏት ማን ናት?

**ሒሳብን በቤት:** ያንሳል፣ ይበልጣል፣ እና እኩል ይሆናል የሚሉ ቃላትን በመጠቀም በቤት ውስጥ የሚገኙ ነገሮችን እንዲያወዳድሩ ልጆችዎን ይጠይቁ፡፡

# ከ11 እስከ 20 ያሉ ቁጥሮችን በቅደም ተከተል ማስቀመጥ

**የመማር ውጤቶች**

- ከ11 እስከ 20 ያሉ ቁጥሮችን በቅደም ተከተል ማስቀመጥ::

የቁጥር መስመር ቁጥሮችን በቅደም ተከተል ለማስቀመጥ ይረዳል::




13 ከ14 ቀድሞ ይገኛል:: ማለትም 13 ከ14 **በፊት** ይገኛል::

15 ከ14 ተከትሎ ይገኛል:: ማለትም 15 ከ14 **በኋላ** ይገኛል::

14 ደግሞ በ13 እና በ15 **መካከል** ይገኛል::

15 ከ14 በ1 ይበልጣል::
13 ደግሞ ከ14 በ1 ያንሳል::

## ምሳሌ

የቁጥር መስመሩን በመጠቀም ጥያቄዎችን መልሱ::






1. ከ17 **በፊት** የሚገኘውን ቁጥር ጻፉ::

2. በ18 እና በ20 **መካከል** የሚገኘውን ቁጥር ጻፉ::

ክፍት ቦታውን የሚያሟላውን ቁጥር ለዩ::




| 3. **በፊት** | 4. **መካከል** | 5. **በፊት** እና **በኋላ** |
|---|---|---|
| ____ ፣ 12 ፣ 13 | 17 ፣ ____ ፣ 19 | ____ ፣ 16 ፣ ____ |
| 6.  | 7.  | 8.  |

## መልመጃ




ክፍት ቦታውን የሚያሟላውን ቁጥር ለዩ።

| 1. በኋላ | 2. በፊት | 3. መካከል |
|---|---|---|
| 11 ፣ 12 ፣ _____ | _____ ፣ 16 ፣ 17 | 13 ፣ _____ ፣ 15 |
| 16 ፣ 17 ፣ _____ | _____ ፣ 15 ፣ 16 | 18 ፣ _____ ፣ 20 |

4. 


5. 


6. 


## ፕሮብሌም መፍታት

1. በ15 እና በ18 መካከል የሚገኙ ሁለት ቁጥሮች እነማን ናቸው?

2. በ11 እና በ14 መካከል የሚገኙ ሁለት ቁጥሮች እነማን ናቸው?

ምስሎችን በመጠቀም ፕሮብሌሙን ፍቱ።

3. እሌኒ 16 አበባዎች አሏት። ሃና ከእሌኒ በ1 የሚያንሱ አበባዎች አሏት። ሳሚያ ደግሞ ከእሌኒ በ1 የሚበልጡ አበባዎች አሏት። የሃና እና የሳሚያ አበባዎች ስንት ናቸው?

ሃና ______ አበባዎች አሏት።

ሳሚያ _____ አበባዎች አሏት።

4. አዜብ በካርቶን ውስጥ 13 ብዮችን ይዛለች። ሮማን ደግሞ ከአዜብ በ2 የሚያንሱ ብዮች አሏት። የሮማን ብዮች ብዛት ስንት ነው? _____ብዮች

**ሒሳብን በቤት:** ከ11 እስከ 20 ያለ አንድ ቁጥር በመውሰድ ልጆችዎ ከዚህ ቁጥር በፊት እና በኋላ የሚመጡትን ቁጥሮች እንዲገልጹ ያድርጉ።

# ከ11 እስከ 20 ያሉ ቁጥሮችን ማወዳደር

**የመማር ውጤቶች**

- ምስሎችን እና ቃላትን በመጠቀም ከ11 እስከ 20 ያሉ ቁጥሮችን ማወዳደር፡፡

ከ1 እስከ 10 ያሉ ቁጥሮችን ማወዳደር ትችላላችሁ፡፡

ከ11 እስከ 20 ያሉትን ቁጥሮች ለማወዳደር

የሚከተለውን ተመልከቱ፡፡



12 ያንሳል ከ14



14 ይበልጣል ከ13



12 እኩል ይሆናል ከ12

## ምሳሌ

ቁጠሩ፡፡ አወዳድሩ፡፡ ትክክለኛ የሆነውን መልስ ምረጡ፡፡

**እስተውሉ**

11 ነጥቦች ከ13 ነጥቦች ያንሳሉ፡፡

1. 

**11** **13**

11 ይበልጣል ከ13 | 11 ያንሳል ከ13 | 11 እኩል ይሆናል ከ13

2. 

18 ___ 16

18 ይበልጣል ከ16 | 18 ያንሳል ከ16 | 18 እኩል ይሆናል ከ16

3. **15** ________ **13**

ይበልጣል | ያንሳል | እኩል ይሆናል

4. **15** ________ **15**

ይበልጣል | ያንሳል | እኩል ይሆናል

5. የትኛው ቁጥር እንደሚበልጥ እንዴት አወቃችሁ? ተወያዩ፡፡

## መልመጃ

ቁጠሩ:: አወዳድሩ:: ትክክለኛ የሆነውን መልስ ምረጡ::

1.  ____ 

15 16

ይበልጣል ያንሳል እኩል ይሆናል

2.  ____ 

20 20

ይበልጣል ያንሳል እኩል ይሆናል

3. 17  ____ 15 

17 ይበልጣል ከ15 17 ያንሳል ከ15 17 እኩል ይሆናል ከ15

ከአወዳደራችሁ በኋላ ትክክለኛ የሆነውን መልስ ምረጡ::

4. 19 ______ 17

ይበልጣል ያንሳል እኩል ይሆናል

5. 12 ________ 16

ይበልጣል ያንሳል እኩል ይሆናል

## ፕሮብሌም መፍታት

1. ከ10 የሚበልጡ ከ20 ግን የሚያንሱ ሁለት ቁጥሮችን ጻፉ:: ከ10 የሚያንሱ ሁለት ቁጥሮችን ጻፉ:: ቁጥሮችን በቅደም ተከተል አስቀምጡ::

2. ገበጣ የኢትዮጵያዊያን ባሕላዊ ጨዋታ ነው:: ከገበጣ መጫዎቻ ገንዳው ግራ እና ቀኝ የተቀመጡትን ብዮች ቁጥር አወዳድሩ:: የትኛው ይበልጣል?



**ሒሳብን በቤት:** አንድ ቁጥር ለምሳሌ 15ን ይውሰዱ:: ልጆችዎ ሦስት ከ15 ያነሱ፤ ሦስት ደግሞ ከ15 የበለጡ ቁጥሮችን እንዲናገሩ ወይም እንዲጽፉ ያድርጉ::

## እስከ 10 ያሉ ቁጥሮችን ማጣመር እና መነጠል

**የመማር ውጤቶች**

- እስከ 10 ያሉ ቁጥሮችን ማጣመር እና መነጠል::

**ዋና ቃላት**

- ማጣመር
- መነጠል

ሁለት የተለያዩ ስብስቦችን በአንድ ላይ መቀላቀል ወይም ማጣመር ይቻላልን? እንደገና ወደ ሁለት መነጠልስ? የሚከተለውን ተመልከቱ::






ከ5 ድመቶች መካከል 3ቱ ይጫዎታሉ:: 2ቱ ደግሞ ወተት ይጠጣሉ::

### ምሳሌ

በእነዚህ ድመቶች ዙሪያ ሌሎች የ5 ተረቶችን ተናገሩ::

1\. 




2\. 



## መልመጃ

1. ስለ 6ቱ ዝንጀሮዎች ተረቶችን ተናገሩ።





2. ስለ 7ቱ ፊኛዎች ተረቶችን ተናገሩ።






3. ሌሎች ጥንድ ቁጥሮችን ፈልጉ።




1 እና 5 ሲጣመሩ 6ን ይሰጣሉ።




4. ሌሎች ጥንድ ቁጥሮችን ፈልጉ።




3 እና 4 ሲጣመሩ 7ን ይሰጣሉ።



**5.** ሌሎች ጥንድ ቁጥሮችን ፈልጉ።




4 እና 4 ሲጣመሩ 8ን ይሰጣሉ።

8 → 4, 4

**6.** ሌሎች ጥንድ ቁጥሮችን ፈልጉ።




7 እና 2 ሲጣመሩ 9ን ይሰጣሉ።

9 → 7, 2

**7.** ሲጣመሩ 10ን የሚሰጡ ሌሎች ጥንድ ቁጥሮችን ፈልጉ።




4 እና 6 ሲጣመሩ 10ን ይሰጣሉ።

10 → 4, 6



ክፍት ቦታውን የሚያሟላውን ቁጥር ለዩ።

**8.** 7 → 5, ☐

**9.** 8 → ☐, 2

10.




11.




12.




13.




## ፕሮብሌም መፍታት

1. አለሙ ቀይ እና ሰማያዊ ቀለማት ያላቸው 16 ወፎችን ተመለከተ። የቀይ እና ሰማያዊ ወፎች ቁጥር እኩል ነው። የቀይ ወፎች እና የሰማያዊ ወፎች ቁጥር ስንት ነው?

2. ህሌና አረንጓዴ እና ቀይ ቀለም ያላቸው 6 እርሳሶች አሏት። የአረንጓዴ እርሳሶች ቁጥር ከቀይ እርሳሶች ቁጥር እጥፍ ነው። ስንት አረንጓዴ እና ስንት ቀይ እርሳሶች አሏት?

3. ኃይሉ 8 የማንጎ ፍራፍሬዎች አሉት። የተወሰኑት ቢጫ ናቸው። የተወሰኑት ደግሞ ብርቱካናማ ናቸው። ስንት ቢጫ እና ስንት ብርቱካናማ ማንጎዎች አሉት?

**ሒሳብን በቤት:** እስከ 10 የሚደርስ አንድ ቁጥር ለምሳሌ 9ን ይውሰዱ። ልጆችዎ ይህን ቁጥር የሚሰጡ ጥንድ ቁጥሮችን እንዲናገሩ ወይንም እንዲጽፉ ያድርጉ።

# የጨዋታ ጊዜ



## ቁጥሮችን የማወዳደር ጨዋታ



| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
|  | 18 ◯ 20 | 19 ◯ 17 | 7 ◯ 9 | 17 ◯ 12 | 19 ◯ 9 |
|  | 10 ◯ 4 | 11 ◯ 19 | 14 ◯ 17 | 13 ◯ 17 | 16 ◯ 12 |
|  | 9 ◯ 9 | 13 ◯ 18 | 8 ◯ 13 | 15 ◯ 14 | 5 ◯ 9 |
|  | 14 ◯ 16 | 19 ◯ 10 | 17 ◯ 12 | 15 ◯ 15 | 13 ◯ 20 |
|  | 11 ◯ 18 | 12 ◯ 11 | 15 ◯ 10 | 2 ◯ 3 | 13 ◯ 13 |
|  | 9 ◯ 8 | 14 ◯ 19 | 13 ◯ 16 | 0 ◯ 1 | 7 ◯ 6 |

**የጨዋታው ህግ፡** በየተራ ዳይ ወርውሩ፡፡ ከወጣው ቁጥር ጋር በሚመሳሰለው ረድፍ በመጀመሪያው ሳጥን ላይ ያሉትን ቁጥሮች አወዳድሩ፡፡ ይበልጣል፣ ያንሳል ወይንም እኩል ይሆናል በማለት ተናገሩ፡፡ ትክክል ከሆናችሁ ሳጥኑን በቦኖ ሸፍኑ፡፡ ከስድስቱ ረድፍ ውስጥ በአንደኛው ረድፍ ላይ ሦስት ሳጥኖችን እስከምትሸፍኑ ድረስ ተጫወቱ፡፡ ሦስቱን ሳጥኖች በቅድሚያ መሸፈን የጨዋታው አሸናፊ ያደርጋል፡፡

# የምዕራፍ ማጠቃለያ መልመጃ

ዓረፍተ ነገሩን የሚያሟሉትን ቃላት ከሳጥኑ ውስጥ ምረጡ፡፡

| ይበልጣል |
|---|
| ያንሳል |
| እኩል ይሆናል |

1. 5 __________ 7፡፡
2. 6 __________ 3፡፡
3. 12 __________ 12፡፡
4. 0 __________ 1፡፡




የቁጥር መስመር በመጠቀም የጎደለውን ቁጥር አሟሉ፡፡

5. በኋላ 3 ፣ ________
6. በፊት ________ ፣ 6

አወዳድሩ፡፡ ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፡፡

7.  6 ይበልጣል / ያንሳል / እኩል ይሆናል  8

8.  6 ይበልጣል / ያንሳል / እኩል ይሆናል  6

9. **8** ______ **8**
ይበልጣል ያንሳል እኩል ይሆናል

10. **5** ______ **3**
ይበልጣል ያንሳል እኩል ይሆናል




የቁጥር መስመር በመጠቀም የጎደለውን ቁጥር አሟሉ፡፡

11. በኋላ ________ ፣14
12. መካከል 18 ፣ ________ ፣ 20

13. 


14. 


15. 


አወዳድሩ፡፡ ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፡፡

16. **18** ________ **17**
ይበልጣል ያንሳል እኩል ይሆናል

17. **12** ________ **13**
ይበልጣል ያንሳል እኩል ይሆናል

የጎደለውን ቁጥር አሟሉ፡፡

**18.**




**19.**




**20.**




**21.**




**22.** 10 ነጭ እና ግራጫ ቀለም ያላቸው ጥንቸሎች አሉ፡፡ ብዛታቸው ተመሳሳይ ቢሆን የነጭ እና ግራጫ ጥንቸሎች ቁጥር ስንት ነው?

_____ ነጭ ጥንቸሎች፣

_____ ግራጫ ጥንቸሎች፡፡

**23.** **እንቆቅልሽ:** እኔ ቁጥር ነኝ፡፡ ከምስል ውስጥ ነኝ፡፡ ከ7 እበልጣለሁ፡፡ ከ12 ግን አንሳለሁ፡፡ ከሦስት ጎን ምስሉ ውስጥ አይደለሁም፡፡ እኔ ማን ነኝ?




**24.** ሶልያና በመጀመሪያው ሳምንት የቅርጫት ኳስ ስልጠና ወቅት ያገኘችውን ነጥብ በሚከተለው መልክ መዘገበች፡፡

| ቀን | ሰኞ | ማክሰኞ | ረቡዕ | ሐሙስ | ዓርብ | ቅዳሜ | እሁድ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ነጥብ | 3 | 4 | 11 | 5 | 1 | 0 | 8 |

የቁጥር መስመር በመጠቀም ሶልያና ያገኘችውን ነጥብ በቅደም ተከተል አስቀምጡ፡፡



# ምዕራፍ 3 እስከ 10 ያሉ ቁጥሮችን መደመር



**የመግቢያ ጥያቄ**

በተሰጠው ምስል ዙሪያ የቁጥር ተረቶችን ተናገሩ፡፡ ዓረፍተ ነገሮችን ጻፉ፡፡

## የቀደመ እውቀታችሁን ከልሱ

በእያንዳንዱ ቡድን ውስጥ ስንት ነገሮች አሉ?

1. 

__________ ሙዝ

2. 

_________ እንቁላሎች

3. 

_________ አበባዎች

ኮርኪ ወይንም ቦኖ በመጠቀም ቁጥሩን ግለጹ፡፡

4. 5
5. 6
6. 3

7. ስንት ቀይ እና ስንት አረንጓዴ ወፎች እንደአሉ ቁጠሩ፡፡ በአጠቃላይ ስንት ወፎች እንደሆኑ ጻፉ፡፡





## የመደመር ተረት

ተረት ታውቃላችሁን? የቁጥር ተረትስ?

የሚከተለውን የቁጥር ተረት ተመልከቱ፡፡



ከጠረጴዛው ላይ 1 ቀይ ቲማቲም አለኝ፡፡ በተጨማሪም 2 ቢጫ ቲማቲሞች አስቀመጥኩ፡፡ በአጠቃላይ በጠረጴዛው ላይ 3 ቲማቲሞች አሉኝ፡፡

**የመማር ውጤቶች**

- የመደመር ጽንሰ-ሐሳብን በተረት መልክ መናገር፡፡

**ዋና ቃላት**

- የቁጥር ተረት
- የመደመር ተረት

### ምሳሌ

በምስሎቹ ዙሪያ አንድ የቁጥር ተረት ለጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

በኖዎችን  በመጠቀም ቁጠሩ፡፡ ቁጥሩን በደብተራችሁ ጻፉ፡፡

1.  _______ ድመቶች

2.  ________ ኤሊዎች

3.  ________ ቢራቢሮዎች

4. ከላይ ያሉት የቁጥር ተረቶች ምን የሚያመሳስላቸው ነገር አለ? ተወያዩ፡፡

## መልመጃ

በምስሎቹ ዙሪያ አንድ የቁጥር ተረት ለጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

ቦኖዎችን በመጠቀም ቁጠሩ፡፡ ቁጥሩን በደብተራችሁ ጻፉ፡፡

1. 

______ ንቦች

2. 

______ ወፎች

3. 

______ ድመቶች

4. የቁጥር ተረት በመፍጠር ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡ ጓደኞቻችሁ ደግሞ ቁጥሩን በመጻፍ ይግለጹ፡፡

## ፕሮብሌም መፍታት

1. 6 ቢጫ እና 3 ብርቱካናማ ቀለም ያላቸው ማንጎዎችን ምስል ሳሉ፡፡ በአጠቃላይ ስንት የማንጎ ምስሎችን ሳላችሁ? በስዕሎቻችሁ ዙሪያ አንድ የቁጥር ተረት ተናገሩ፡፡

2. ከት/ቤታችን ጣሪያ ላይ 4 ቀይ ወፎች አሉ፡፡ ሌሎች የተወሰኑ ሰማያዊ ወፎች ተቀላቀሏቸው፡፡ ከት/ቤታችን ጣሪያ ላይ ስንት ሰማያዊ ወፎች አሉ? አብራሩ፡፡

**ሒሳብን በቤት:** ለልጆችዎ የመደመር ተረት ይናገሩ፡፡ ቦኖዎችን፣ ሳንቲሞችን ወይንም የልብስ አዝራሮችን በመጠቀም ልጆችዎ ተረቱን እንዲወክሉ ያድርጉ፡፡

## የመደመር ዓረፍተ ነገር

**የመማር ውጤቶች**

- ምልክቶችን በመጠቀም የመደመር ዓረፍተ ነገር መጻፍ፡፡

**ዋና ቃላት**

- መደመር፣ እኩል ይሆናል፣ ድምር፣ የመደመር ዓረፍተ ነገር

**ተመልከቱ** 

**በቦኖ ወክሉ** 

**ተናገሩ** 3 **ሲደመር** 2 **እኩል ይሆናል** 5

**ጻፉ** 3 + 2 = 5

3 + 2 = 5 **የመደመር ዓረፍተ ነገር** ነው፡፡

5 የ3 እና የ2 **ድምር** ነው፡፡

ድምር በአጠቃላይ ስንት እንደሆኑ ይገልጻል፡፡



### ምሳሌ

በቦኖ ወክሉ፡፡ የመደመር ዓረፍተ ነገሩን በደብተራችሁ ጻፉ፡፡

1. 

   2 ሲደመር 2 እኩል ይሆናል 4

   2 + 2 = 4

2. 

   ____ + ____ = ____

3. 

   ____ + ____ = ____

4. 

   ____ + ____ = ____

5. በመደመር ዓረፍተ ነገር ውስጥ ድምሩ የትኛው እንደሆነ እንዴት መለየት ይቻላል? ተወያዩ፡፡

## መልመጃ

ድምሩን ለማግኘት ሁሉንም በአንድ ላይ ቁጠሩ።

የመደመር ዓረፍተ ነገሩን በደብተራችሁ ጻፉ።

1. 

____ + ____ = ____

2. 

____ ◯ ____ ◯ ____

3. 

____ ◯ ____ ◯ ____

4. 

____ ◯ ____ ◯ ____

5. 

____ ◯ ____ ◯ ____

6. 

____ ◯ ____ ◯ ____



## ፕሮብሌም መፍታት

1. 1 + 4 = 5 የሚለውን የመደመር ዓረፍተ ነገር የሚወክለው የቱ ነው?







2. ሔለን 5 የመጫወቻ መኪናዎች አሏት። ማርታ ደግሞ 4 መኪናዎች አሏት። በአጠቃላይ የሁለቱ ጓደኞች ስንት መኪናዎች አሏቸው?

____ ◯ ____ ◯ ____ 

3. ሁነኛው ከምሳ በፊት 2 ብርጭቆ ውሃ ጠጣ። ከምሳ በኋላ ደግሞ 3 ብርጭቆ ውሃ ጠጣ። በአጠቃላይ ስንት ብርጭቆ ውሃ ጠጣ?

____ ◯ ____ ◯ ____ 

**ሒሳብን በቤት:** ለልጆችዎ የመደመር ተረት ይናገሩ። ተረቱን የሚወክል የመደመር ዓረፍተ ነገር እንዲጽፉ ያድርጉ።

## ዜሮን መደመር

**የመማር ውጤቶች**
- ከማንኛውም ቁጥር ላይ ዜሮን መደመር

ከማንኛውም ቁጥር ላይ ዜሮን ብትደምሩ ድምሩ ምን ይሆናል? የሚከተለውን ተመልከቱ፡፡

5 ባርኔጣዎች ነበሩ፡፡
ምንም ባርኔጣ አልተጨመረም፡፡



5 + 0 = 5

አሁንም 5 ባርኔጣዎች አሉ፡፡

መጀመሪያ ምንም ባርኔጣ አልነበረም፡፡



0 + 3 = 3

በአጠቃላይ 3 ባርኔጣዎች አሉ፡፡

### ምሳሌ

ድምሩን ፈልጉ፡፡

1.  0 + 5 = 5

2.  6 + 0 = ______

3.  7 + 0 = ____

4.  0 + 8 = ______

ክቦችን በመሳል ቁጥሩን አሳዩ፡፡ ድምሩን ፈልጉ፡፡

5. 8 + 0 = ____
6. 7 + 3 = ____
7. 0 + 9 = ____

8. ሁለቱም ተደማሪዎች ዜሮ ቢሆኑ ድምሩ ምን ይሆናል? ተወያዩ፡፡

## መልመጃ

ድምሩን ፈልጉ፡፡

1.  0 + 6 = ______

2.  3 + 0 = ______

3.  ____ + ____ = ____

4.  ____ + ____ = ____

| | | |
|---|---|---|
| 5. 6 + 2 = _____ | 6. 8 + 0 = _____ | 7. 2 + 0 = _____ |
| 8. 2 + 3 = _____ | 9. 0 + 7 = _____ | 10. 0 + 5 = _____ |

## ፕሮብሌም መፍታት

1. ትንቢት የሚከተለውን የመደመር ዓረፍተ ነገር ጻፈች፡፡




ትንቢት ለምን ስህተት እንደሰራች ተናገሩ፡፡ አስተካክላችሁ ጻፉ፡፡

3. 2 ተማሪዎች የትምህርት ቤታቸውን አጥር ቀለም እየቀቡ ነው፡፡ 3 ተጨማሪ ተማሪዎች ሊያግዟቸው ተቀላቀሉ፡፡ በአጠቃላይ ስንት ልጆች አጥሩን ቀለም እየቀቡ ነው?

____ ◯ ____ ◯ ____ ተማሪዎች

4. በሠፈራችን መጫዎቻ ሜዳ ላይ ምንም ህፃን አልነበረም፡፡ 6 ህፃናት ቅርጫት ኳስ ለመጫዎት ወደ ሜዳው ገቡ፡፡ ስንት ህፃናት በሜዳው ላይ አሉ?

____ ◯ ____ ◯ ____ ህፃናት

**ሒሳብን በቤት:** በአንድ እጅዎ የተወሰኑ የአንድ ብር ሳንቲም ይያዙ፡፡ ሁለቱንም እጅዎን ወደ ልጆችዎ በመዘርጋት የትኛው እጅዎ ዜሮ ሳንቲም እንደያዘ ይጠይቁ፡፡ ድምሩን ይፈልጉ፡፡

# በመደመር 4ን፣ 5ን፣ እና 6ን ማግኘት

**የመማር ውጤቶች**

- በመደመር 4ን፣ 5ን እና 6ን ለማግኘት የተለያዩ መንገዶችን መለየት::

በመደመር 4ን ለማግኘት ከአንድ በላይ መንገዶች አሉን? ቀጣዩን የልጆችን ስራ ተመልከቱ::




## ምሳሌ

1. ቦኖዎችን ●● በመጠቀም 4ን በመደመር የማግኘት መንገዶችን ፈልጉ:: በደብተራችሁ ላይ ክቦችን ◯ በመሳል ቀለም ቀቡ:: የመደመር ዓረፍተ ነገሩን አሟሉ::

| በመደመር 4ን የማግኘት መንገዶች | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ● | ሲደመር | ● | እኩል ይሆናል | ድምር |
| ●●●● | 1 | + | 3 | = | 4 |
| ○○○○ | ___ | + | ___ | = | 4 |
| ○○○○ | ___ | + | ___ | = | 4 |

2. 4ን የሚያሳየውን ምስል ለዩ::



3. በመደመር 4ን የማግኛ ሌላ ያልተገለጸ መንገድ አለን? ተወያዩ::

## መልመጃ

1. ቦኖዎችን 🔴🟡 በመጠቀም 5ን በመደመር የማግኛ መንገዶችን ለዩ:: በደብተራችሁ ላይ ክቦችን ◯ በመሳል ቀለም ቀቡ:: የመደመር ዓረፍተ ነገሩን አሟሉ::

| በመደመር 5ን የማግኘት መንገዶች | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | 🔴 | ሲደመር | 🟡 | እኩል ይሆናል | ድምር |
| ◯◯◯◯◯ | ___ | + | ___ | = | 5 |
| ◯◯◯◯◯ | ___ | + | ___ | = | 5 |
| ◯◯◯◯◯ | ___ | + | ___ | = | 5 |
| ◯◯◯◯◯ | ___ | + | ___ | = | 5 |

2. ቦኖዎችን 🔴🟡 በመጠቀም 6ን በመደመር የማግኘት መንገዶችን ለዩ:: በደብተራችሁ ላይ ክቦችን ◯ በመሳል ቀለም ቀቡ:: የመደመር ዓረፍተ ነገሩን አሟሉ::

| በመደመር 6ን የማግኘት መንገዶች | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | 🔴 | ሲደመር | 🟡 | እኩል ይሆናል | ድምር |
| ◯◯◯◯◯◯ | ___ | + | ___ | = | 6 |
| ◯◯◯◯◯◯ | ___ | + | ___ | = | 6 |
| ◯◯◯◯◯◯ | ___ | + | ___ | = | 6 |

## ፕሮብሌም መፍታት

መሰለች 3ን የማግኛ መንገዶችን በሚከተለው መልክ በጥቁር ሠሌዳው ላይ ጻፈች:: መሰለች ትክክል ናትን?




**ሒሳብን በቤት:** ለልጆችዎ 6 ነገሮችን ይስጡ:: ከዚያም በመደመር 4ን፣ 5ን እና 6ን የማግኛ ሁሉንም መንገዶች እንዲያሳዩ ያድርጉ::

## በመደመር 7ን፣ 8ን፣ 9ን እና 10ን ማግኘት

**የመማር ውጤቶች**

- በመደመር 7ን፣ 8ን፣ 9ን እና 10ን የማግኛ የተለያዩ መንገዶችን መለየት።

7ን ፣ 8ን ፣ 9ን እና 10ን በመደመር የማግኛ የተለያዩ መንገዶችን ማሳየት ትችላላችሁን?

የሚከተለውን ተመልከቱ።



1 + 6 = 7

2 + 6 = 8

3 + 6 = 9

4 + 6 = 10

ሌሎች መንገዶችም አሉ አይደል?

### ምሳሌ

1. ቦኖዎችን  በመጠቀም 7ን እና 8ን በመደመር የማግኛ መንገዶችን አሳዩ። ዓረፍተ ነገሩን ጻፉ።

**በመደመር 7ን የማግኛ መንገዶች**

|  | ሲደመር |  | እኩል ይሆናል | ድምር |
|---|---|---|---|---|
| 1 | + | 6 | = | 7 |
| ____ | + | ____ | = | 7 |
| ____ | + | ____ | = | 7 |
| ____ | + | ____ | = | 7 |
| ____ | + | ____ | = | 7 |
| ____ | + | ____ | = | 7 |

**በመደመር 8ን የማግኛ መንገዶች**

|  | ሲደመር |  | እኩል ይሆናል | ድምር |
|---|---|---|---|---|
| 1 | + | 7 | = | 8 |
| ____ | + | ____ | = | 8 |
| ____ | + | ____ | = | 8 |
| ____ | + | ____ | = | 8 |
| ____ | + | ____ | = | 8 |
| ____ | + | ____ | = | 8 |

2. በመደመር 7ን እና 8ን የማግኛ ሌሎች መንገዶች አሉን? ተወያዩ።

## መልመጃ

በኖዎችን በመጠቀም 9ን እና 10ን በመደመር የማግኛ መንገዶችን አሳዩ። ዓረፍተ ነገሩን ጻፉ።

| በመደመር 9ን የማግኛ መንገዶች | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | ሲደመር | | እኩል ይሆናል | ድምር |
| ____ | + | ____ | = | 9 |
| ____ | + | ____ | = | 9 |
| ____ | + | ____ | = | 9 |
| ____ | + | ____ | = | 9 |
| ____ | + | ____ | = | 9 |
| ____ | + | ____ | = | 9 |
| ____ | + | ____ | = | 9 |

| በመደመር 10ን የማግኛ መንገዶች | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | ሲደመር | | እኩል ይሆናል | ድምር |
| ____ | + | ____ | = | 10 |
| ____ | + | ____ | = | 10 |
| ____ | + | ____ | = | 10 |
| ____ | + | ____ | = | 10 |
| ____ | + | ____ | = | 10 |
| ____ | + | ____ | = | 10 |
| ____ | + | ____ | = | 10 |

## ፕሮብሌም መፍታት

1. እንድሪስ 11ን የማግኛ መንገዶችን በሚከተለው መልክ በጥቁር ሠሌዳው ላይ ጽፏል።
ትክክል ያልሆነው አለን? ለምን?
ስህተቱን አስተካክሉ። ሌሎች መንገዶችንም ለዩ።




2. አያቴ 9 አበባዎች አሏት። በቀዩ እና በአረንጓዴው የአበባ ማስቀመጫዎቿ በእያንዳንዳቸው ስንት አበባዎችን ማስቀመጥ ትችላለች?



**ሒሳብን በቤት:** ለልጆችዎ 10 ነገሮችን (ለምሳሌ 10 የአንድ ብር ሳንቲም) ይስጡ። ከዚያም በሳንቲሞቹ የዘውድ እና የቁጥር ገጽ በመጠቀም 7ን፣ 8ን፣ 9ን እና 10ን የማግኛ ሁሉንም መንገዶች እንዲያሳዩ ያድርጉ።

## ቁልቁል መደመር

**የመማር ውጤቶች**

- የመደመር ዓረፍተ ነገርን በቁልቁል መጻፍ፡፡

ቁጥሮችን ስትደምሩ የመደመር ዓረፍተ ነገሩን እንዴት ነው የምትጽፉት? ከግራ ወደ ቀኝ በአግድም በመደርደር ነው፡፡ በሌላ መንገድ ለምሳሌ ቁልቁል በመደርደር መግለጽ ይቻላልን? የሚከተለውን ተመልከቱ፡፡



4 + 3 = 7

ድምር

በአግድም መደመር

$$\begin{array}{r} 4 \\ +\ 3 \\ \hline 7 \end{array}$$

ድምር



የነጥቦቹ ቁጥር ተመሳሳይ ነው አይደል? ስለዚህ ድምሩ ተመሳሳይ ነው፡፡

በቁልቁል መደመር

### ምሳሌ

ቁጥሮችን በደብተራችሁ ጻፉ፡፡ ደምሩ፡፡

**1.**



3 + 2 = 5

+



**2.**



____+____=____

+



**3.**



____+____=____

+



**3.** በአግድም ወይም ቁልቁል መደመር ልዩነት አለውን? ተወያዩ፡፡

## መልመጃ

ቁጥሮችን በደብተራችሁ ጻፉ:: ደምሩ::

1. 

____ + ____ = ____



$$\begin{array}{r} \square \\ + \square \\ \hline \square \end{array}$$

2. 

____ + ____ = ____



$$\begin{array}{r} \square \\ + \square \\ \hline \square \end{array}$$

3. 

____ + ____ = ____



$$\begin{array}{r} \square \\ + \square \\ \hline \square \end{array}$$

## ፕሮብሌም መፍታት

1. አምሳል 6ን እና 3ን በጥቁር ሰሌዳው ላይ በሚታየው መልክ ደመረች::አምሳል ለምን እንደተሳሳተች ተናገሩ::




2. ድምሮችን ፈልጉ:: በአገኛችሁት ውጤት መሰረት ቀጣዩን የመደመር ዓረፍተ ነገር አሟሉ::

$$\begin{array}{r} 1 \\ +\ 4 \\ \hline \square \end{array} \qquad \begin{array}{r} 2 \\ +\ 4 \\ \hline \square \end{array} \qquad \begin{array}{r} 3 \\ +\ 4 \\ \hline \square \end{array} \qquad \begin{array}{r} 4 \\ +\ 4 \\ \hline \square \end{array} \qquad \begin{array}{r} \square \\ + \square \\ \hline \square \end{array}$$

**ሒሳብን በቤት:** ለልጆችዎ የመደመር ዓረፍተ ነገር ይስጡ:: ከዚያም ልጆችዎ በአግድም እና በቁልቁል እንዴት መደመር እንደሚቻል ያሳዩ::

## በማንኛውም ቅደም ተከተል መደመር

**የመማር ውጤቶች**

- በማንኛውም ቅደም ተከተል ድምርን መፈለግ::

**ዋና ቃላት**

- ተደማሪ
- ድምር

በመደመር ዓረፍተ ነገር ውስጥ **ተደማሪ** የሚባሉት የትኞቹ ናቸው? **ድምር** የሚባለውስ የትኛው ነው? ቁጥሮችን ስትደምሩ የተደማሪዎችን ቅደም ተከተል ብታቀያይሩት ድምሩ ላይ ለውጥ ያመጣልን?

የሚከተለውን ተመልከቱ::



3 + 5 = 8

ተደማሪ ተደማሪ ድምር



5 + 3 = 8

ስለዚህ የተደማሪዎችን ቅደም ተከተል ብታቀያይሩትም ተመሳሳይ ድምር ታገኛላችሁ ማለት ነው::

3 + 5 = 5 + 3

### ምሳሌ

ተደማሪዎችን በደብተራችሁ ጻፉ:: ቦኖዎችን ተጠቀሙ:: ደምሩ::

1. 

2 + 5 = 7



___ + ___ = ___

2. 

$\square + \square = \square$



$\square + \square = \square$

ደምሩ::

3. 9 + 1 = ___    1 + 9 = ___

4. 
$$\begin{array}{r} 2 \\ +\ 7 \\ \hline \square \end{array} \qquad \begin{array}{r} 7 \\ +\ 2 \\ \hline \square \end{array}$$

5. 5 + 7 = ___    7 + 5 = ___

6. በማንኛውም ቅደም ተከተል መቀነስ ትችላላችሁን? ተወያዩ::

## መልመጃ

ተደማሪዎችን በደብተራችሁ ጻፉ። ቦኖዎችን ተጠቀሙ። ደምሩ።

1. 

4 + 5 = 9



___ + ___ = ___

2. 

ደምሩ።

3. 3 + 8 = ___ 8 + 3 = ___

5. 6 + 4 = ___ 4 + 6 = ___

4.

$$\begin{array}{r} 8 \\ +\ 6 \\ \hline \square \end{array} \qquad \begin{array}{r} 6 \\ +\ 8 \\ \hline \square \end{array}$$

## ፕሮብሌም መፍታት

1. የአብዱ እናት 7 ደብተር ገዛችለት። አባቱ ደግሞ 6 ተጨማሪ ደብተር ገዛለት። በአጠቃላይ ስንት ደብተር እንደተገዛለት የሚያሳይ ሁለት የመደመር ዓረፍተ ነገር ጻፉ።

2. ወደ ትምህርት ቤት ከመሄዴ በፊት 30 ደቂቃ አለኝ። መኝታ ክፍሌን ለማሰናዳት 20 ደቂቃ፤ ቦርሳየን ደግሞ 10 ደቂቃ ይወስድብኛል። ሁለቱንም ተግባራት ለማከናወን በቂ ጊዜ አለኝን? መጀመሪያ የትኛውን ተግባር ማከናወን ይኖርብኛል? ለምን?

**ሒሳብን በቤት:** ለልጆችዎ ሁለት ቁጥሮችን (ለምሳሌ 4ን እና 9ን) ይስጡ። በእነዚህ ቁጥሮች ላይ ተመስርተው ሁለት የመደመር ዓረፍተ ነገር እንዲጽፉ ያድርጉ።

## ወደፊት በመቁጠር መደመር

**የመማር ውጤቶች**

- ወደፊት እየጨመሩ በመቁጠር ድምር መፈለግ::

**ዋና ቃል**

- ወደፊት መቁጠር

ወደፊት 1ን ፣ 2ን ፣ 3ን እየጨመሩ በመቁጠር እንዴት መደመር እንደሚቻል ታውቃላችሁን?

የሚከተለውን ተመልከቱ::

በሳጥኑ ውስጥ 5 ኩቦች ነበሩ:: 2 ኩቦችን ጨመርኩበት::

አሁን ላይ በሳጥኑ ውስጥ ስንት ኩቦች አሉ?

5 + 2 = 7




6 ፣ 7




### ምሳሌ

ኩቦችን ተጠቀሙ:: ከትልቁ ቁጥር ጀምሩ:: ወደፊት በመቁጠር ደምሩ::

1. 


7 ፣ 8 ፣ 9

6 + 3 = _____

2. 


_____ ፣ _____ ፣ _____

3 + 8 = _____

3. 


____ ፣ ____ ፣ ____

3 + 5 = _____

4. 


_____ ፣ _____

7 + 2 = _____

5. 


_____

7 + 1 = _____

6. 


_____ ፣ _____

8 + 2 = _____

7. ወደፊት ስትቆጥሩ ከትልቁ ቁጥር ለምን ትጀምራላችሁ? ተወያዩ::

## መልመጃ

ኩቦችን ተጠቀሙ:: ከትልቁ ቁጥር ጀምሩ:: ወደፊት በመቁጠር ደምሩ::

1.



____ ፣ ____ ፣ ____

9 + 3 = ____

2.



____ ፣ ____

2 + 9 = ____

3.



____ ፣ ____

7 + 2 = ____

4.



____ ፣ ____ ፣ ____

3 + 6 = ____

ኩቦችን ተጠቀሙ:: ከትልቁ ቁጥር ጀምሩ:: ወደፊት በመቁጠር ደምሩ::

| | | |
|---|---|---|
| 5. 3 + 7 = ____ | 6. 2 + 9 = ____ | 7. 2 + 3 = ____ |
| 8. 9 + 1 = ____ | 9. 1 + 7 = ____ | 10. 8 + 3 = ____ |
| 11. 4<br>+ 1 | 12. 9<br>+ 3 | 13. 2<br>+ 8 |

## ፕሮብሌም መፍታት

1. ልዑል 9 ቢራቢሮዎችን ከአበባዎች ላይ ተመለከተ:: 3 ተጨማሪ ቢራቢሮዎች ተቀላቀሏቸው:: ምን ያክል ቢራቢሮዎች ከአበባዎች ላይ አሉ?
ወደፊት በመቁጠር እንዴት ፕሮብሌሙን መፍታት እንደሚቻል አብራሩ?

2. ሙሉነሽ ከካርቶን ውስጥ 12 እርሳሶችን አወጣች:: አያሌው ደግሞ ከሙሉነሽ በ3 የሚበልጡ እርሳሶችን አወጣ:: አያሌው ስንት እርሳሶች ከካርቶኑ ውስጥ አወጣ?

**ሒሳብን በቤት:** ልጆችዎ ወደፊት በመቁጠር የ3ን እና የ8ን ድምር ይፈልጉ::

## አስር በመሙላት መደመር

**የመማር ውጤቶች**

- አስር በመሙላት የመደመር ዘዴን በመጠቀም ድምርን መፈለግ፡፡

**ዋና ቃል**

- አስር መሙላት

ቁጥሮችን ከ10 ጋር በቀላሉ መደመር ይቻላል፡፡ ስለዚህ ሁለት ቁጥሮችን ስትደምሩ አንደኛውን ቁጥር 10 እንዲሞላ ብታደርጉ ድምሩን ለመፈለግ ይቀላል ማለት ነው፡፡

የሚከተለውን አስር በመሙላት የመደመር ዘዴ ተመልከቱ፡፡





9 + 4 እኩል ይሆናል 10 + 3፡፡

### ምሳሌ

በኖዎችን  ተጠቀሙ፡፡ ድምሩን ፈልጉ፡፡

1. 

9 + 5 = 14 ፣ ምክንያቱም

10 + 4 = 14

2. 

8 + 4 = ______ ፣ ምክንያቱም

10 + 2 = ______

3. 

8 + 5 = _____ ፣ ምክንያቱም

10 + 3 = _____

4. 

9 + 3 = ______ ፣ ምክንያቱም

10 + 2 = ______

5. መደመርን በቀላሉ ለማስላት አስር መሙላት ለምን አስፈለገ? ተወያዩ፡፡

## መልመጃ

መጀመሪያ ትልቁን ቁጥር 10 መሙላት::

በኖዎችን ተጠቀሙ:: ድምሩን ፈልጉ::

1. 

8 + 6 = ______ ፣ ምክንያቱም

10 + 4 = ______

2. 

9 + 6 = _____ ፣ ምክንያቱም

10 + 5 = ______

3. 9 + 7 = _____ ፣ ምክንያቱም
10 + 6 =_______

4. 8 + 7 = _____ ፣ ምክንያቱም
10 + 5 = ______

5. 7 + 5 = _____ ፣ ምክንያቱም

10 + ______= ______

6. 8 + 3 = ______ ፣ ምክንያቱም

10 + ______ = ______

## ፕሮብሌም መፍታት

9 + 6 = _____

10 + 6 = 16

1. ቢኒያም የ9 እና የ6 ድምርን ለመፈለግ በሚከተለው መንገድ ሰርቷል:: የቢኒያም ስህተት የቱ ላይ ነው? አስተካክላችሁ ጻፉ::

2. በውሃ ኩሬ ውስጥ 8 እንቁራሪቶች ነበሩ:: 7 ተጨማሪ እንቁራሪቶች ወደ ኩሬው ተቀላቀሉ:: በኩሬው ውስጥ ስንት እንቁራሪቶች አሉ?
አስር በመሙላት እንዴት ፕሮብሌሙን መፍታት እንደሚቻል አብራሩ?

3. ናርዶስ መክሰስ ከመመገቧ በፊት ከመጽሐፏ ላይ 9 ገጾችን አነበበች:: ከመክሰስ በኋላ ደግሞ 8 ተጨማሪ ገጾችን አነበበች:: በአጠቃላይ ስንት ገጾችን አነበበች?

**ሒሳብን በቤት:** ልጆችዎ ትናንሽ ነገሮችን ለምሳሌ ጠጠር በመጠቀም 9 + 4 እና 10 + 3 እንዴት ተመሳሳይ ሊሆኑ እንደቻሉ እንዲያብራሩ ያድርጉ::

## በእጥፍ በማስላት መደመር

**የመማር ውጤቶች**
- በእጥፍ በማስላት መደመር ::

**ዋና ቃል**
- በእጥፍ ማስላት

በእጥፍ ማስላት ማለት ምን ማለት ነው?

በእጥፍ በማስላት ድምርን መፈለግ ይቻላል።

የሚከተለውን ተመልከቱ።

5 + 5 = 10

ሁሉም ተደማሪዎች ተመሳሳይ ናቸው።

5 + 6 = 11

በእጥፍ ካሰላችሁ በኋላ 1 መጨመር።

### ምሳሌ

የመደመር ዓረፍተ ነገሩን አሟሉ። ኩቦችን ተጠቀሙ።

1. 4 + 4 = 8
2. 4 + 5 = 9
3. ____ + ____ = 12
4. ____ + ____ = 13

ድምሩን ወይንም ተደማሪውን ጻፉ።

5. 3 + 3 = ____
6. 3 + 4 = ____
7. 5 + ____ = 10



8. $\begin{array}{r} 7 \\ +\ 7 \\ \hline \end{array}$
9. $\begin{array}{r} 7 \\ +\ 8 \\ \hline \end{array}$
10. $\begin{array}{r} 2 \\ +\ 8 \\ \hline \end{array}$

11. 4 + 4ን ማወቅ 4 + 5ን ለመፈለግ እንዴት ሊያግዝ ይችላል? ተወያዩ።

## መልመጃ



የመደመር ዓረፍተ ነገሩን አሟሉ፡፡ ኩቦችን ተጠቀሙ፡፡

1. 

_____ + _____ = _____

2. 

_____ + _____ = _____

3. 

_____ + _____ = _____

4. 

_____ + _____ = _____

ድምሩን ወይንም ተደማሪውን ጻፉ፡፡

5. 1 + 1 = _______

6. 1 + 2 = _______

7. _____ + 4 = 8

8. $\begin{array}{r} 6 \\ +\ 6 \\ \hline \end{array}$

9. $\begin{array}{r} 7 \\ +\ 6 \\ \hline \end{array}$

10. $\begin{array}{r} 3 \\ +\ 6 \\ \hline \end{array}$

## ፕሮብሌም መፍታት

1. ዮርዳኖስ በሁለት ረድፍ 14 ችግኞችን ተከለች፡፡ 7 ችግኞችን በመጀመሪያው ረድፍ ተከለች፡፡ በሁለተኛው ረድፍ ስንት ተከለች?

2. ሰይድ 6 እርግቦችን ተመለከተ፡፡ ሳምራዊት ደግሞ 7 እርግቦችን ተመለከተች፡፡ በአጠቃላይ ሁለቱም ጓደኞች ስንት እርግቦችን ተመለከቱ?

_____ ◯ _____ = _____

3. ሐና 10 የዶሮ እግሮችን በአጥሩ ስር ተመለከተች፡፡ ምን ያክል ዶሮዎች አሉ?



**ሒሳብን በቤት:** ልጆችዎ በእጥፍ ማስላትን ሊገልጹ የሚችሉ ነገሮችን (ለምሳሌ የሁለቱም እጅ እና እግር ጣቶች) ተጠቅመው ድምር እንዲፈጉ ያድርጉ፡፡

# የጨዋታ ጊዜ



## ድምሩን ወይም ተደማሪውን የማሟላት ጨዋታ



| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
|  | 4 + 7 =___ | ___+ 9 =12 | 5 +___ =15 | 3 + 6 =___ | 9 +___ =16 |
|  | ___+ 6 =16 | 9 + 2 =___ | 10+___ =18 | ___+ 6 =12 | 5 + 8 =___ |
|  | 9 +___ =17 | ___+ 7 =14 | 5 + 7 =___ | ___+11 =18 | 8 +___ =17 |
|  | 6 + 7 =___ | ___+10 =20 | 5 +___ =11 | 4 + 9 =___ | ___+ 5 =14 |
|  | 2 +___ =10 | 9 + 9 =___ | 15+___ =20 | ___+ 7 =16 | 6 + 7 =___ |
|  | 7 +___ =12 | ___+ 5 =13 | 2 + 9 =___ | ___+ 6 =15 | 10+___ =19 |

**የጨዋታው ህግ፡** በየተራ ዳይ ወርውሩ፡፡ ከወጣው ቁጥር ጋር በሚመሳሰለው ረድፍ በመጀመሪያው ሳጥን ላይ ያለውን ዓ/ነገር አሟሉ፡፡ መልሱን ለጓደኞችሁ ተናገሩ፡፡ ትክክል ከሆናችሁ ሳጥኑን በቦና ሸፍኑ፡፡ ከስድስቱ ረድፍ ውስጥ በአንደኛው ረድፍ ላይ ሦስት ተከታታይ ሳጥኖችን እስከምሸፍኑ ድረስ ተጫዎቱ፡፡ የጨዋታው አሸናፊ ሦስቱን ሳጥኖች በቅድሚያ የሸፈነ/ች ይሆናል፡፡

# የምዕራፍ ማጠቃለያ መልመጃ

**አዛምዱ**

| | |
|---|---|
| 1. የመደመር ዓፍተ ነገር | ሀ) + |
| 2. እኩል ይሆናል | ለ) 1 + 2 = 3 |
| 3. ዜሮ | ሐ) = |
| 4. መደመር | መ) 0 |

**በምስሎቹ ዙሪያ የቁጥር ተረት ለጓደኞቻችሁ ተናገሩ። ዓረፍተ ነገሩን ጻፉ።**



5. ____ ◯ ____ ◯ ____



6. ____ ◯ ____ ◯ ____

**የመደመር ዓረፍተ ነገሩን ጻፉ።**



7. ____ ◯ ____ ◯ ____



8. ____ ◯ ____ ◯ ____



9. ____ ◯ ____ ◯ ____



10. ____ ◯ ____ ◯ ____



11. ____ ◯ ____ ◯ ____



12. ____ ◯ ____ ◯ ____

ደምሩ

| | | |
|---|---|---|
| 13. 1 + 6 = ______ | 14. 9 + 0 = ______ | 15. 3 + 2 = ______ |
| 16. 4 + 4 = ______ | 17. 5 + 1 = ______ | 18. 0 + 3 = ______ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 19. 3 + 1 = ☐ | 20. 2 + 6 = ☐ | 21. 3 + 5 = ☐ | 22. 4 + 4 = ☐ |

ክቦችን ◯ ቀለም ቀቡ:: የመደመር ዓረፍተ ነገሩን አሟሉ::

23. ◯◯◯◯◯

____ + ____ = 5

24. ◯◯◯◯◯

____ + ____ = 5

ክቦችን ◯ በመሳል 10ን የማግኛ ዘዴዎችን አሳዩ:: ቁጥሮችን ጻፉ::

25.

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | | | |
| | | | | |

____ + ____ = 10

26.

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | | | |
| | | | | |

____ + ____ = 10

27. ትህትና ወደ ትምህርት ቤት ስትሄድ 4 መጽሐፍት ይዛለች:: ሐብታሙ ደግሞ 8 መጽሐፍት ይዟል:: በአጠቃይ ሁለቱ ተማሪዎች ስንት መጽሐፍት ይዘዋል?

28. አብዱ 5 ወፎችን ከት/ቤታቸው ግቢ ውስጥ ከሚገኝ ዛፍ ላይ ተመለከተ:: ጀማል ደግሞ 3 ወፎችን ተመለከተ:: በአጠቃላይ ሁለቱ ጓደኛሞች ስንት ወፎችን ተመለከቱ?

29. አስቴር 5 ብዮች አሏት:: የብዮቹ ቁጥር 12 እንዲሆንላት ምን ያክል ተጨማሪ ብዩች ያስፈልጋታል?

30. የተወሰኑ ዳክየዎች በኩሬው ውስጥ እየዋኙ ነው:: 3 ተጨማሪ ዳክየዎች ወደ ኩሬው ለመዋኘት ገቡ:: ከዚያም 9 ዳክየዎች በመዋኘት ላይ ናቸው:: መጀመሪያ በኩሬው ውስጥ ስንት ዳክየዎች ሲዋኙ ነበር? እንዴት እንዳገኛችሁት አብራሩ::

# ምዕራፍ 4 እስከ 10 ያሉ ቁጥሮችን መቀነስ



**የመግቢያ ጥያቄ**

ስንት ወፎች አያችሁ? ስንት ወፍ በረረ? ስንት ወፎች ይቀራሉ?

## የቀደመ እውቀታችሁን ከልሱ

1. ዱባዎቹ ስንት ናቸው?



2. ወፎቹ ስንት ናቸው?



ክቦችን በመጠቀም ቁጥሩን በምስል ግለጹ፡፡

3. 4

4. 3

5. 6

6. 3 አሳዎችን በቀይ ቦና ሸፍኑ፡፡ ያልተሸፈኑት አሳዎች ስንት እንደሆኑ በደብተራችሁ ጻፉ፡፡



## የመቀነስ ተረቶች

**የመማር ውጤቶች**

- የመቀነስ ጽንሰ-ሐሳብን በተረት መልክ መናገር::

**ዋና ቃላት**

- የመቀነስ ተረት

ተረት ታውቃላችሁን? ተማሪ ሳሙኤል የሚከተለውን የቁጥር ተረት ለክፍል ጓደኞቹ ነገራቸው::

> ከጠረጴዛው ላይ 5 እርሳሶች ነበሩኝ:: 1 እርሳስ ለጓደኛየ ሰጠኂት:: ከጠረጴዛው ላይ 4 እርሳሶች ይቀሩኛል::



በመቁጠር ማረጋገጥ ይቻላል::

### ምሳሌ

በምስሎቹ ዙሪያ አንድ የቁጥር ተረት ለጓደኛችሁ ተናገሩ:: ቁጠሩ:: ቁጥሩን በደብተራችሁ ጻፉ::

1. ስንት እንቁራሪቶች ከቅጠሉ ላይ ቀሩ?



________ እንቁራሪቶች

2. ስንት ወፎች ከጎጆው ውስጥ ቀሩ?



________ወፎች

3. ስንት ፍየሎች ከሳሩ ላይ ተኝተዋል? ስንቶቹ ተነስተው ሄዱ? ከሳሩ ላይ ስንት ቀሩ?



_______ ፍየሎች



_________ ፍየሎች



________ ፍየሎች

4. የመደመር እና የመቀነስ ተረቶች የሚለያዩት እንዴት ነው? ተወያዩ::

## መልመጃ

በምስሎቹ ዙሪያ አንድ የቁጥር ተረት ለጓደኛችሁ ተናገሩ። ቁጠሩ። ቁጥሩን በደብተራችሁ ጻፉ።

1. ከቅጠሉ ላይ ስንት ጢንዚዛዎች ቀሩ?



_________ጢንዚዛዎች

2. ስንት ቅጠሎች ከዛፉ ላይ ቀሩ?



_________ቅጠሎች

3. ስንት ቢራቢሮዎች ከአበቦቹ ላይ ቀሩ?



_________ቢራቢሮዎች

4. ስንት አፕሎች ከዛፉ ላይ ቀሩ?



_________አፕሎች

## ፕሮብሌም መፍታት

1. በንብ ቀፎው ዙሪያ 8 ንቦች ይገኛሉ።
   4ቱ አበባ ለመቅሰም በረው ሄዱ።
   ምን ያክል ንቦች በቀፎው ዙሪያ ቀሩ?



______ንቦች

2. የራሳችሁን የቁጥር ተረት በመፍጠር ለጓደኞቻችሁ ንገሩ። ተረቱን ስዕል በመሳል አሳዩ። ጓደኞቻችሁ ደግሞ ተረቱን እንዲመልሱ ጠይቋቸው።

**ሒሳብን በቤት:** ለልጆችዎ የመቀነስ ተረት ይናገሩ። ቦኖዎችን፣ ሳንቲሞችን ወይንም የልብስ አዝራሮችን በመጠቀም ልጆችዎ ተረቱን እንዲወክሉ ያድርጉ።

## የመቀነስ ዓረፍተ ነገር

**የመማር ውጤቶች**
- ምልክቶችን በመጠቀም የመቀነስ ዓረፍተ ነገርን መጻፍ::

**ዋና ቃላት**
- መቀነስ
- እኩል ይሆናል
- ልዩነት
- የመቀነስ ዓረፍተ ነገር

***ተመልከቱ***



***በቦኖ ወክሉ***



***ተናገሩ*** 5 **ሲቀነስ** 2 **እኩል ይሆናል** 3

***ጻፉ*** 5 — 2 = 3

5 — 2 = 3 **የመቀነስ ዓረፍተ ነገር** ነው::

3 **ልዩነት** ይባላል::

የX ምልክት ያልተደረገባቸው ነገሮች ልዩነትን ያሳያሉ::

— የመቀነስ ምልክት ነው::

= የእኩል ይሆናል ምልክት

### ምሳሌ

የመቀነስ ዓረፍተ ነገሩን ጻፉ::

1. 

   5 ሲቀነስ 3 እኩል ይሆናል 2::

   5 − 3 = 2

2. 

   ____ − ____ = ____

3. 

   ____ ○ ____ ○ ____

4. 

   ____ ○ ____ ○ ____

5. የX ምልክት የተደረገባቸው ነገሮች ምንን ያሳያሉ? ተወያዩ::

## መልመጃ

የመቀነስ ዓረፍተ ነገሩን በደብተራችሁ ጻፉ።

1. 

____ ◯ ____ ◯ ____

2. 

____ ◯ ____ ◯ ____

3. 

____ ◯ ____ ◯ ____

4. 

____ ◯ ____ ◯ ____

5. 

____ ◯ ____ ◯ ____

6. 

____ ◯ ____ ◯ ____

## ፕሮብሌም መፍታት

1. 10 ተማሪዎች በአውቶቡስ ውስጥ ነበሩ። 7 ተማሪዎች መንገድ ላይ ወረዱ። በአውቶቡሱ ውስጥ ስንት ተማሪዎች ቀሩ? የቁጥር ዓረፍተ ነገሩን ጻፉ።

2. የመሰለች እናት 16 ገጽ ያለው የተረት መጽሐፍ ገዛች። መሰለች በመጀመሪያው ቀን 7 ገጾችን አነበበች። መጽሐፉን አንብባ ለመጨረስ ምን ያክል ገጾች ይቀራታል?

3. ለምለም 6 ካሮት ነበሯት። የተወሰኑትን ለሁሴን ሰጠችው። አሁን 2 ካሮት ይቀሯታል። ለሁሴን የሰጠችው ምን ያክል ካሮት ነው? ________ ካሮት

**ሒሳብን በቤት:** ለልጆችዎ በኖዎችን፣ ሳንቲሞችን ወይንም የልብስ አዝራሮችን በመጠቀም የመቀነስ ዓረፍተ ነገር እንዲጽፉ ያድርጉ።

## ዜሮን መቀነስ እና ሁሉንም መቀነስ

ከማንኛውም ቁጥር ላይ ዜሮን ብትቀንሱ ልዩነቱ ምን እንደሚሆን ታውቃላችሁን? ሁሉንም ብትቀንሱስ? የሚከተለውን ተመልከቱ::

**የመማር ውጤቶች**
- ዜሮን መቀነስ::
- ዜሮ ልዩነትን መፈለግ::

**ዋና ቃላት**
- ዜሮ
- ዜሮ ልዩነት



3 – 0 = 3

ዜሮን ስትቀንሱ ምን ቀራችሁ?

ሁሉም አለ::



3 – 3 = 0

ሁሉንም ስትቀንሱ ምን ቀራችሁ?

ምንም አልቀረም::

**አስተውሉ**

ሁሉንም ስትቀንሱት ዜሮ ይቀራል:: ዜሮን ስትቀንሱ ሁሉም ይቀራል::

### ምሳሌ

ልዩነቱን ፈልጉ:: የመቀነስ ዓረፍተ ነገሩን ጻፉ::

1. 

   5 – 5 = 0

2. 

   ____ ◯ ____ ◯ ____

3. 

   ____ ◯ ____ ◯ ____

4. 

   ____ ◯ ____ ◯ ____

ልዩነቱን ፈልጉ::

5. 8 – 0 = ______
6. 9 — 3 = ______
7. 4 — 4 = ______

8. ሁሉንም ስትቀንሱ ልዩነቱ ለምን ዜሮ ይሆናል? ተወያዩ::

## መልመጃ

**ልዩነቱን ፈልጉ። የመቀነስ ዓረፍተ ነገሩን ጻፉ።**

1. 

____ ◯ ____ ◯ ____

2. 

____ ◯ ____ ◯ ____

3. 

____ ◯ ____ ◯ ____

4. 

____ ◯ ____ ◯ ____

**ልዩነቱን ፈልጉ።**

5. 1 — 0 = ____
6. 9 — 9 = ____
7. 4 — 2 = ____
8. 3 — 0 = ____
9. 6 — 1 = ____
10. 2 — 0 = ____

## ፕሮብሌም መፍታት

1. 11 የእግር ኳስ ተጨዋቾች ከመልበሻ ክፍል ነበሩ። ሁሉም ተጨዋቾች ወደ መጫዎቻ ሜዳው እየሮጡ ገቡ። ከመልበሻ ክፍሉ ውስጥ ምን ያክል ተጨዋቾች ቀሩ? የቁጥር ዓረፍተ ነገሩን ጻፉ። ____ ◯ ____ ◯ ____

2. ሃና 6 ብርቱካኖች ነበሯት። 3 ብርቱካኖችን ለአለሙ ሰጠችው። 3ቱን ደግሞ ለሒክማ ሰጠቻት። ሃና ስንት ብርቱካኖች ቀሯት? ________ብርቱካኖች

**ሒሳብን በቤት:** ለልጆችዎ 3 ነገሮችን በመስጠት 3 — 0 እና 3 — 3 እንዲያሳዩ ያድርጉ።

## ከ4፣ ከ5 እና ከ6 ላይ መቀነስ

**የመማር ውጤቶች**

- ከ4 ፣ ከ5 እና ከ6 ላይ የመቀነስ መንገዶችን መለየት።

ከአንድ ቁጥር ላይ ለመቀነስ የተለያዩ መንገዶች እንዳሉ ታውቃላችሁን? የሚከተለውን ተመልከቱ።

ከ4 ላይ 2ን መቀነስ እችላለሁ።
**4 - 2 = 2**
ልዩነቱ 2 ነው።



ከ4 ላይ 1ን መቀነስ እችላለሁ።
**4 - 1 = 3**
ልዩነቱ 3 ነው።

### ምሳሌ

1. በቦኖዎች ● ምስል ላይ የX ምልክት በማድረግ ከ4 ላይ የመቀነስ መንገዶችን አሳዩ። የመቀነስ ዓረፍተ ነገሩን አሟሉ።

| ከ4 ላይ የመቀነስ መንገዶች | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ● | ሲቀነስ | ● | እኩል ይሆናል | ልዩነት |
| ● ● ● ⊗ | 4 | − | 1 | = | 3 |
| ● ● ● ● | 4 | − | ___ | = | ___ |
| ● ● ● ● | 4 | − | ___ | = | ___ |
| ● ● ● ● | 4 | − | ___ | = | ___ |

2. የሚከተለውን የአበባ ምስል ሳሉ። ከ4 ላይ በዙሪያው ያሉትን ቁጥሮች ቀንሱ። ልዩነቱን ከአበባዋ ውጫዊ ክፍል ላይ ጻፉ።

ዓረፍተ ነገሮችን ጻፉ።




___ ○ ___ ○ ___    ___ ○ ___ ○ ___

3. በመቀነስ ላይ ልዩነት ማለት ምን ማለት ነው? ተወያዩ።

## መልመጃ

1. ቦኖዎችን 🔴 በመጠቀም ከ5 እና ከ6 ላይ የመቀነስ መንገዶችን አሳዩ:: ዓረፍተ ነገሩን አሟሉ::

| ከ5 ላይ የመቀነስ መንገዶች | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 🔴 | ሲቀነስ | 🔴 | እኩል ይሆናል | ልዩነት |
| 5 | − | ____ | = | ____ |
| 5 | − | ____ | = | ____ |
| 5 | − | ____ | = | ____ |
| 5 | − | ____ | = | ____ |

| ከ6 ላይ የመቀነስ መንገዶች | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 🔴 | ሲቀነስ | 🔴 | እኩል ይሆናል | ልዩነት |
| 6 | − | ____ | = | ____ |
| 6 | − | ____ | = | ____ |
| 6 | − | ____ | = | ____ |
| 6 | − | ____ | = | ____ |

ልዩነቱን ፈልጉ::

2. 6 — 1 =____
3. 5 — 0 =____
4. 5 — 2 =____
5. 5 — 5 =____
6. 4 — 2 =____
7. 6 — 0 =____



## ፕሮብሌም መፍታት

1. ከፍያለው ከ3 ላይ የመቀነስ መንገዶችን በሚከተለው መልክ ጻፈ:: ከፍያለው ትክክል ነውን? ለምን?




2. ሳምያ 5 የተምር ፍሬዎች አሏት:: ለእህቷ ልታካፍል የምትችልበትን ሁሉንም መንገዶች ዘርዝሩ::

3. ሐና 6 ብርቱካኖች ነበሯት:: ከ1 በላይ ብርቱካኖችን ብትመገብ ስንት ብርቱካን ይቀራታል? መልሱን ያገኘችሁበትን ሁሉንም የመቀነስ ዓረፍተ ነገሮች ጻፉ::

**ሒሳብን በቤት:** ለልጆችዎ 6 ነገሮችን ይስጡ:: ከዚያም ከ4 ላይ፣ ከ5 ላይ እና ከ6 ላይ የመቀነስ ሁሉንም መንገዶች እንዲያሳዩ ያድርጉ::

# ከ7 ፣ ከ8 ፣ ከ9 እና ከ10 ላይ መቀነስ

**የመማር ውጤቶች**

- ከ7፣ ከ8፣ ከ9 እና ከ10 ላይ የመቀነስ መንገዶችን መለየት።

ከ7 ላይ የመቀነስ የተለያዩ መንገዶች እንዳሉ ታውቃላችሁን? የሚከተለውን ተመልከቱ።

ከ7 ላይ 3ን ቀነስኩ።
7 — 3 = 4
ልዩነቱ 4 ነው።



ከ7 ላይ 4ን ቀነስኩ።
7 — 4 = 3
ልዩነቱ 3 ነው።

## ምሳሌ

1. ቦኖዎችን ● በመጠቀም ከ7 እና ከ8 ላይ የመቀነስ መንገዶችን አሳዩ። ልዩነቱን ፈልጉ። ዓረፍተ ነገሩን አሟሉ።

**ከ7 ላይ የመቀነስ መንገዶች**

| ● | ሲቀነስ | ● | እኩል ይሆናል | ልዩነት |
|---|---|---|---|---|
| 7 | − | 1 | = | 6 |
| 7 | − | ____ | = | ____ |
| 7 | − | ____ | = | ____ |
| 7 | − | ____ | = | ____ |
| 7 | − | ____ | = | ____ |

**ከ8 ላይ የመቀነስ መንገዶች**

| ● | ሲቀነስ | ● | እኩል ይሆናል | ልዩነት |
|---|---|---|---|---|
| 8 | − | ____ | = | ____ |
| 8 | − | ____ | = | ____ |
| 8 | − | ____ | = | ____ |
| 8 | − | ____ | = | ____ |
| 8 | − | ____ | = | ____ |

2. የሚከተለውን የአበባ ምስል ሳሉ። ከ7 ላይ በዙሪያው ያሉትን ቁጥሮች ቀንሱ። ልዩነቱን ከአበባዋ ውጫዊ ክፍል ላይ ጻፉ። ዓረፍተ ነገሮችን ጻፉ።

____ ◯ ____ ◯ ____     ____ ◯ ____ ◯ ____




3. ከ7 እና ከ8 ላይ የመቀነስ ሌሎች ያልተገለጹ መንገዶች አሉን? ተወያዩ።

## መልመጃ

1. ቦኖዎችን 🔴 በመጠቀም ከ9 እና ከ10 ላይ የመቀነስ መንገዶችን አሳዩ:: ልዩነቱን ፈልጉ:: ዓረፍተ ነገሩን አሟሉ::

| ከ9 ላይ የመቀነስ መንገዶች | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 🔴 | ሲቀነስ | 🔴 | እኩል ይሆናል | ልዩነት |
| 9 | − | ____ | = | ____ |
| 9 | − | ____ | = | ____ |
| 9 | − | ____ | = | ____ |
| 9 | − | ____ | = | ____ |
| 9 | − | ____ | = | ____ |
| 9 | − | ____ | = | ____ |

| ከ10 ላይ የመቀነስ መንገዶች | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 🔴 | ሲቀነስ | 🔴 | እኩል ይሆናል | ልዩነት |
| 10 | − | ____ | = | ____ |
| 10 | − | ____ | = | ____ |
| 10 | − | ____ | = | ____ |
| 10 | − | ____ | = | ____ |
| 10 | − | ____ | = | ____ |
| 10 | − | ____ | = | ____ |

ልዩነቱን ፈልጉ:: በደብተራችሁ ጻፉ::

| | | |
|---|---|---|
| 2. 7 — 4 = _____ | 3. 8 — 4 = _____ | 4. 9 — 8 = _____ |
| 5. 8 — 5 = _____ | 6. 9 — 4 = _____ | 7. 7 — 3 = _____ |

## ፕሮብሌም መፍታት



1. እየሩስ 3 እንቁራሪቶችን በእጇ መዳፍ ያዘች:: 2ቱ ዘለው ውሃ ውስጥ ገቡ:: እየሩስ ምን ያክል እንቁራሪቶች አሁን ላይ አሏት? _______ እንቁራሪቶች

2. መልሰው የተወሰኑ መጽሐፍት ነበሩት:: 2 መጽሐፍትን ለእህቱ ሰጣት:: አሁን ላይ 6 መጽሐፍት ቀርተውታል:: መልሰው መጀመሪያ ምን ያክል መጽሐፍት ነበሩት? _________ መጽሐፍት



**ሒሳብን በቤት:** ለልጆችዎ 10 ነገሮችን ይስጡ:: እነዚህን ነገሮች በመጠቀም ከ10 ላይ የመቀነስ ሁሉንም መንገዶችን እንዲያሳዩ ያድርጉ:: ልዩነቱንም እንዲናገሩ ያድርጉ::

## ቁልቁል መቀነስ

**የመማር ውጤቶች**

- የመቀነስ ዓረፍተ ነገርን በቁልቁል መጻፍ።

የመቀነስ ዓረፍተ ነገርን ቁልቁል በመደርደር መግለጽ ይቻላልን? የሚከተለውን ተመልከቱ።



7 − 3 = **4**

ልዩነት

በአግድም መቀነስ



$$\begin{array}{r} 7 \\ -\ 3 \\ \hline 4 \end{array}$$

ልዩነት

በቁልቁል መቀነስ

የX ምልክት ያልተደረገባቸው ነጥቦች ቁጥር ተመሳሳይ ነው። ስለዚህ ልዩነቱ ተመሳሳይ ነው።

### ምሳሌ

የመቀነስ ዓረፍተ ነገሩን አሟሉ። በደብተራችሁ ጻፉ።

1\.



8 − 3 = _____



$$\begin{array}{r} 8 \\ -\ 3 \\ \hline \square \end{array}$$

2\.

$$\begin{array}{r} 9 \\ -\ 4 \\ \hline \square \end{array}$$

9 − 4 = _____

### መልመጃ

የመቀነስ ዓረፍተ ነገሩን አሟሉ። በደብተራችሁ ጻፉ።

1\.



11 − 5 = _____



$$\begin{array}{r} 11 \\ -\ 5 \\ \hline \square \end{array}$$

2\.

$$\begin{array}{r} 6 \\ -\ 1 \\ \hline \square \end{array}$$

6 − 1 = _____

### ፕሮብሌም መፍታት

ከጠረጴዛ ላይ 10 ብርቱካኖች አሉ። ለምለም 2ቱን ተመገበች። ምን ያክል ቀሩ? የቁጥር ዓረፍተ ነገሩን በአግድም እና በቁልቁል በደብተራችሁ ጻፉ።

**ሒሳብን በቤት:** 12 ትናንሽ ነገሮችን በመጠቀም መቀነስን ልጆችዎ እንዲያሳዩ ያድርጉ። የመቀነስ ዓረፍተ ነገሩን በአግድም እና ቁልቁል በመደርደር እንዲጽፉ ያድርጉ።

## ወደኋላ በመቁጠር መቀነስ

**የመማር ውጤቶች**

- ወደ ኋላ እየቀነሱ በመቁጠር ልዩነትን መፈለግ፡፡

**ዋና ቃላት**

- ወደ ኋላ መቁጠር

ወደኋላ በ1 እየቀነሱ በመቁጠር ልዩነትን መፈለግ እንደሚቻል ታውቃላችሁን?

የሚከተለውን ተመልከቱ፡፡

በሳጥኖቹ ውስጥ 8 ድመቶች ነበሩ፡፡




7 ፣ 6

2 ድመቶች ወጥተው ሄዱ፡፡

8 — 2 = 6

በሳጥኑ ውስጥ 6 ድመቶች ቀሩ፡፡




7 ፣ 6 ፣ 5

3 ድመቶች ወጥተው ሄዱ፡፡

8 — 3 = 5

በሳጥኑ ውስጥ 5 ድመቶች ቀሩ፡፡

### ምሳሌ

ወደኋላ በመቁጠር ቀንሱ፡፡ በደብተራችሁ ጻፉ፡፡

1. 


8 ፣ 7

9 — 2 = ____

2. 


____ ፣ ____ ፣ ____

9 — 3 = ____

3. 8 — 1 = ______

8፣ ______

4. 7 — 2 = ______

7፣ ______ ፣ ______

5. 4 — 1 = ______
6. 6 — 3 = ______
7. 6 — 2 = ______
8. 4 — 2 = ______
9. 7 — 3 = ______
10. 4 — 3 = ______
11. በምትቀንሱበት ጊዜ ለምን ወደ ኋላ ትቆጥራላችሁ? ተወያዩ፡፡

## መልመጃ

ወደኋላ በመቁጠር ቀንሱ:: በደብተራችሁ ጻፉ::

1. 


_____ ፣ _____

10 — 2 = _____

2. 


_____ ፣ _____ ፣ _____

10 — 3 = _____

ከ10 ጀምሩ:: ወደኋላ 3 ቁጠሩ::

3. 6 — 2 = _______

6፣ ______ ፣ ______

4. 11 — 3 = _______

11፣ ______ ፣ ______ ፣ ______

| | | |
|---|---|---|
| 5. 11 — 2 = _____ | 6. 9 — 1 = _____ | 7. 12 — 3 = _____ |
| 8. 5 — 3 = _____ | 9. 3 — 2 = _____ | 10. 10 — 3 = _____ |

## ፕሮብሌም መፍታት

1. በጣና ሐይቅ ዳርቻ 12 ጀልባዎች ነበሩ:: 3ቱ ጀልባዎች ጎብኝዎችን ይዘው በሐይቁ ላይ መጓዝ ጀመሩ:: ከሐይቁ ዳርቻ ስንት ጀልባዎች ቀሩ? _______ ጀልባዎች

2. በመጫዎቻ ሜዳው ላይ 9 ተማሪዎች ይጫወታሉ:: 5 ተማሪዎች ወደ ክፍል ገቡ:: በመጫዎቻ ሜዳው ላይ ስንት ተማሪዎች ቀሩ? _______ ተማሪዎች

3. አሳ አጥማጅ ከጣና ሐይቅ 15 አሳዎችን ያዘ:: እድገታቸውን ያልጨረሱትን 5 አሳዎች ወደ ሐይቁ መለሳቸው:: ስንት አሳዎች ቀሩት? _______ አሳዎች

**ሒሳብን በቤት:** በወረቀት ላይ 14 - 3 = _____ ብለው ይጻፉ:: ልጆችዎ ወደኋላ መቁጠር ዘዴን በመጠቀም ልዩነቱን እንዲፈልጉ ያድርጉ::

## የመደመር እና የመቀነስ ዝምድና

**የመማር ውጤቶች**

- የመደመርን እና የመቀነስን ዝምድና በመጠቀም ፕሮብሌሞችን መፍታት፡፡

**ዋና ቃላት**

- የዝምድና እውነታዎች

4 + 9 =13 እንደሆነ ታውቃላችሁን?

ይህን የመደመር እውነታ ተጠቅማችሁ

13 – 9ን እና 13 – 4ን መፈለግ ትችላላችሁ፡፡

የሚከተለውን ተመልከቱ፡፡

$$\begin{array}{r}4\\+9\\\hline 13\end{array}\qquad\begin{array}{r}13\\-\ 9\\\hline 4\end{array}\qquad\begin{array}{r}13\\-\ 4\\\hline 9\end{array}$$

### ምሳሌ

የመደመር እና የመቀነስ የዝምድና እውነታዎችን በመጠቀም ዓረፍተ ነገሮችን አሟሉ፡፡

1. $\begin{array}{r}3\\+8\\\hline 11\end{array}\qquad\begin{array}{r}11\\-3\\\hline 8\end{array}$

2. $\begin{array}{r}6\\+\ 5\\\hline \square\end{array}\qquad\begin{array}{r}11\\-\ 6\\\hline \square\end{array}$

3. $\begin{array}{r}6\\+\ 4\\\hline \square\end{array}\qquad\begin{array}{r}10\\-\ 6\\\hline \square\end{array}$

የመደመር እውነታዎችን በመጠቀም የመቀነስ ዓረፍተ ነገሮችን ጻፉ፡፡

4. 4 + 7 = 11
   11 – 4 = 7
   11 – 7 = 4

5. 7 + 6 = _____
   _____ – _____ = _____
   _____ – _____ = _____

6. 8 + 4 = _____
   _____ – _____ = _____
   _____ – _____ = _____

ቁጥሮችን በመጠቀም የመደመር እና የመቀነስ ዝምድና እውነታዎችን ጻፉ፡፡

7. **9 ፧ 7 ፧ 2**

   2 + 7 = 9    7 + 2 = 9

   9 – 2 = 7    9 – 7 = 2

   9፣ 7 እና 2 የአንድ ቤተሰብ ቁጥሮች ናቸው፡፡

8. **4 ፧ 8 ፧ 12**

   8 + 4 = _____    _____ + _____ = _____

   _____ – _____ = _____    _____ – _____ = _____

9. 1 + 5 = 6 እና 6 – 1 = 5 ዝምድና አላቸውን? እንዴት? ተወያዩ፡፡

## መልመጃ

የመደመር እና የመቀነስ የዝምድና እውነታዎችን በመጠቀም ዓረፍተ ነገሮችን አሟሉ፡፡ በደብተራችሁ ጻፉ፡፡

1. 6 + 4 = ☐ 10 − 4 = ☐

2. 6 + 5 = ☐ 11 − 5 = ☐

3. 3 + 8 = ☐ 11 − 8 = ☐

የመደመር እውነታዎችን በመጠቀም የመቀነስ ዓረፍተ ነገሮችን ጻፉ፡፡

4. 6 + 7 = ____
 ____ − ____ = ____
 ____ − ____ = ____

5. 4 + 8 = ____
 ____ − ____ = ____
 ____ − ____ = ____

6. 7 + 4 = ____
 ____ − ____ = ____
 ____ − ____ = ____

የሚከተሉትን ቁጥሮች በመጠቀም የመደመር እና የመቀነስ የዝምድና እውነታዎችን በደብተራችሁ ጻፉ፡፡

7. **1 ፣ 9 ፣ 10**
 1 + 9 = ____  ____ + ____ = ____
 ____ − ____ = ____  ____ − ____ = ____

8. **9 ፣ 7 ፣ 16**
 7 + 9 = ____  ____ ◯ ____ = ____
 ____ ◯ ____ = ____  ____ ◯ ____ = ____

## ፕሮብሌም መፍታት

በምስሉ በሚታዩት አፕሎች ላይ ተመስርታችሁ አራት የዝምድና እውነታዎችን ጻፉ፡፡



____ ◯ ____ = ____  ____ ◯ ____ = ____
____ ◯ ____ = ____  ____ ◯ ____ = ____

**ሒሳብን በቤት:** ለልጆችዎ የአንድ ቤተሰብ ቁጥሮችን ለምሳሌ 5 ፣ 9 እና 14ን ይስጡ፡፡ ልጆችዎ ሁለት የመደመር እና ሁለት የመቀነስ ዓረፍተ ነገሮችን እንዲጽፉ ያድርጉ፡፡

# የጨዋታ ጊዜ

## የመቀነስ ጨዋታ






**አስፈላጊ ቁሶች:** ዳይ እና ቦኖዎች ወይንም ኮርኪዎች

**የጨዋታው ህግ:** በየተራ ዳይ ወርውሩ፡፡ በወጣው ቁጥር መሰረት ተጓዙ፡፡ በአረፋችሁበት ቦታ ያለውን የመቀነስ ዓረፍተ ነገር ስሩ ከዚያም ቦኖአችሁን አስቀምጡበት፡፡ ስትቀንሱ ስህተት ከሰራችሁ ቦኖውን ወደ ቀደመ ቦታው መልሱ፡፡ በቀጣይ ዙር ካላችሁበት ቦታ በመቀጠል ቁጠሩ፡፡ ዝንጀሮው ይወዳችኋል፡፡ አዞው ግን አይወዳችሁም፡፡ ቀድሞ መጨረሻ ቦታ ላይ መድረስ የጨዋታው አሸናፊ ያደርጋል፡፡

## የምዕራፍ ማጠቃለያ መልመጃ

**አዛምዱ**

| | |
|---|---|
| 1. የመቀነስ ዓረፍተ ነገር | ሀ) – |
| 2. እኩል ይሆናል | ለ) 1 + 2 = 3 |
| 3. መቀነስ | ሐ) = |
| 4. ልዩነት | መ) + |
| | ሠ) 7 – 5 = 2 |

5. የመደመር እና የመቀነስ ዝምድና እውነታዎችን የሚያሳየውን ለዩ።

ሀ) 7 + 3 = 10    10 – 3 = 7
3 + 7 = 10    10 – 7 = 3

ለ) 6 + 4 = 10    5 + 5 = 10
4 + 6 = 10    8 + 2 = 10

በምስሎቹ ዙሪያ አንድ የቁጥር ተረት ለጓደኞቻችሁ ተናገሩ። ዓረፍተ ነገሩን በደብተራችሁ ጻፉ።

6.


____ ○ ____ ○ ____

7.


____ ○ ____ ○ ____

ልዩነቱን ፈልጉ። የመቀነስ ዓረፍተ ነገሩን በደብተራችሁ ጻፉ።

8. 

____ ○ ____ ○ ____

9. 

____ ○ ____ ○ ____

10. 

____ ○ ____ ○ ____

11. 

____ ○ ____ ○ ____

**ልዩነቱን ፈልጉ። በደብተራችሁ ጻፉ።**

| | | |
|---|---|---|
| **12.** 10 – 9 = ______ | **13.** 8 – 3 = ______ | **14.** 4 – 4 = ______ |
| **15.** 7 – 2 = ______ | **16.** 9 – 5 = ______ | **17.** 10 – 1 = ______ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| **18.** 9 − 0 = ☐ | **19.** 7 − 1 = ☐ | **20.** 5 − 2 = ☐ | **21.** 3 − 3 = ☐ |

**22.** የውሻዋ ልጅ (ቡችላዋ) ወደ ቤቷ እንድትደርስ አቅጣጫዋን በመጠቆም አግዙ። ስህተት የሆነውን የቁጥር ዓረፍተ ነገር ለዩ። ሁሉም የቁጥር ዓረፍተ ነገሮች ትክክል የሆኑበትን አቅጣጫ ተከተሉ። ትክክል በሆነው አቅጣጫ በቦኖ ምልክት አስቀምጡ።



23. 8 ተማሪዎች በትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ ካለ ሜዳ ላይ ይጫዎቱ ነበር። 4ቱ ተማሪዎች ወደ ቤተ መጻሕፍት ክፍል ሄዱ። ስንት ተማሪዎች በሜዳው ላይ ቀሩ?

_________ ተማሪዎች

24. ሁሴን 7 ማንጎዎችን ተመገበ። መኮነን ደግሞ 3 ማንጎዎችን ተመገበ። ሁሴን የተመገበው የማንጎ ብዛት መኮነን ከተመገበው በስንት ይበልጣል?

___________ማንጎዎች

25. 8 ጉንዳኖች ምግብ በማሰባሰብ ስራ ላይ ነበሩ። የተወሰኑ ተጨማሪ ጉንዳኖች ወደ ስራው ተቀላቀሉ። በአጠቃላይ 17 ጉንዳኖች በስራ ላይ አሉ። ወደ ስራው የተቀላቀሉት ተጨማሪ ጉንዳኖች ስንት ናቸው? ሁሉንም የመደመር እና የመቀነስ ዓረፍተ ነገሮችን ጻፉ።

___________ጉንዳኖች

26. ሰናይት 12 እርሳሶች አሏት። 5ቱ እርሳሶች ቀይ ቀለም አላቸው። የቀሩት ደግሞ ቢጫ ናቸው። ቢጫ ቀለም ያላቸው እርሳሶች ስንት ናቸው? እንዴት እንዳገኛችሁት አብራሩ።

# ምዕራፍ 5 ጊዜ



**የመግቢያ ጥያቄ**

በትምህርት ቤታችሁ የሰንደቅ ዓላማ ሥነ-ሥርዓት የሚካሄደው ምን ሰዓት ላይ ነው?

## የቀደመ እውቀታችሁን ከልሱ

1. ትንሽ ጊዜ ሊወስድባችሁ የሚችለውን ተግባር ለዩ፡፡





2. ብዙ ጊዜ ሊወስድባችሁ የሚችለውን ተግባር ለዩ፡፡





ቀጥሎ የሚመጣውን ቁጥር ለዩ፡፡

3. 5 ፣ 6 ፣ 7 ፣ ____

4. 12 ፣ 11 ፣ 10 ፣ ____

5. እኔ ከ10 ተከትየ (በኋላ) እገኛለሁ፡፡ ከ12 ደግሞ ቀድሜ (በፊት) እገኛለሁ፡፡ እኔ ስንት ቁጥር ነኝ?

## የድርጊቶች ቅደም ተከተል

**የመማር ውጤቶች**
- ድርጊቶችን በቅደም ተከተል ማስቀመጥ::

**ዋና ቃላት**
- ጠዋት፣ ከሰዓት፣ ምሽት
- በፊት፣ በኋላ፣ መካከል

**ጠዋት** ፣ **ከሰዓት** እና **ምሽት** ምንን እንደሚገልጹ ታውቃላችሁ? በእነዚህ ጊዜያት ምን ታደርጋላችሁ? የሚከተለውን ተመልከቱ::

**ጠዋት** **ከሰዓት** **ምሽት**







**ጠዋት** ፣ **ከሰዓት** እና **ምሽት** በቀን ውስጥ ያሉ ጊዜያት ናቸው::

ሰላማዊት ትምህርት ቤት ከመሄዷ **በፊት** ቁርስ ትበላለች::

ሰሎሜ እራት ከበላች **በኋላ** ጥርሷን ትቦርሻለች::

ሱሌማን ከትምህርት ቤት ከተመለሰ **በኋላ** መጽሐፍ ያነባል::

### ምሳሌ

የምትከውኑትን ድርጊት ግለጹ::

1. **ጠዋት**
2. **ከሰዓት**
3. **ምሽት**

4. ወደ ትምህርት ቤት ከመሄዳችሁ **በፊት** ምን ታደርጋላችሁ? ትምህርት ቤት ምሳ ከተመገባችሁ **በኋላ** ምን ታደርጋላችሁ? ተወያዩ::

## መልመጃ

የምትከውኑትን ድርጊት ግለጹ፡፡

| 1. ከምሳ በፊት | 2. ከምሳ በኋላ |
| --- | --- |
| | |

| 3. ከትምህርት ቤት በፊት | 4. ከትምህርት ቤት በኋላ |
| --- | --- |
| | |

## ፕሮብሌም መፍታት

የሚከተሉትን ምስሎች በቅደም ተከተል አስቀምጡ፡፡ መጀመሪያ፣ ሁለተኛ፣ ሦስተኛ በማለት መልሱ፡፡







**ሒሳብን በቤት:** ልጆችዎ በትምህርት ቤት የተከወነ አንድ ድርጊት እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡ ከዚያ ድርጊት በፊት እና በኋላ የተከወኑ ድርጊቶችን እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡

## ጊዜ በሰዓት ሲገለጽ

**የመማር ውጤቶች**

- ጊዜን በሰዓት መጻፍ እና መናገር፡፡

**ዋና ቃላት**

- ሰዓት፣ የሰዓት ጠቋሚ
- ደቂቃ፣ የደቂቃ ጠቋሚ

የግድግዳ ሰዓት ቆጣሪ አይታችሁ ታውቃላችሁን?

ከ1 እስከ 12 ያሉ ቁጥሮችን ይዟል፡፡

የሚከተለውን ተመልከቱ፡፡




የሰዓት ጠቋሚው ከ5 ላይ ይጠቁማል፡፡ የደቂቃ ጠቋሚው ደግሞ 12 ላይ አርፏል፡፡ ስለዚህ **5 ሰዓት** ነው፡፡

**የሰዓት ጠቋሚው** አጠር ያለ ነው፡፡ ስንት ሰዓት እንደሆነ ይጠቁማል፡፡ **የደቂቃ ጠቋሚው** ደግሞ ረዘም ያለ ነው፡፡ ስንት ደቂቃ እንደሆነ ይጠቁማል፡፡

**ምሳሌ**

የሰዓት ጠቋሚው ያረፈው ከ2 ላይ ነው፡፡ የደቂቃ ጠቋሚው ደግሞ ከ12 ላይ ነው፡፡

የሰዓት ቆጣሪውን ተጠቀሙ፡፡ ሰዓቱን ጻፉ፡፡

1.  2 ሰዓት

2.  _____ ሰዓት

3.  _____ ሰዓት

4.  _____ ሰዓት

5. በሰዓት ጠቋሚ እና በደቂቃ ጠቋሚ መካከል ምን ልዩነት አለ? ተወያዩ፡፡

## መልመጃ

የሰዓት ቆጣሪውን ተጠቀሙ:: ሰዓቱን በደብተራችሁ ጻፉ::

1.  _____ ሰዓት

2.  _____ ሰዓት

3.  _____ ሰዓት

4.  _____ ሰዓት

5.  _____ ሰዓት

6.  _____ ሰዓት

## ፕሮብሌም መፍታት

1. ዳግም 12 ሰዓት ላይ ከመኝታው ተነሳ:: ሰይድ ደግሞ ከ1 ሰዓት በኋላ ተነሳ:: ሰይድ ከመኝታው ስንት ሰዓት ላይ ተነሳ?



_____ ሰዓት

2. ጨዋታው 3 ሰዓት ላይ ተጀመረ:: ከ2 ሰዓት በኋላ ተጠናቀቀ:: ጨዋታው ስንት ሰዓት ላይ ተጠናቀቀ?

**ሒሳብን በቤት:** ልጆችዎ ከ1 ሰዓት ጀምሮ በቅደም ተከተል ጊዜን በሰዓት እንዲቆጥሩ ያድርጉ::

## ጊዜ በግማሽ ሰዓት ሲገለጽ

**የመማር ውጤቶች**

- ጊዜን በግማሽ ሰዓት መጻፍ እና መናገር።

**ዋና ቃላት**

- ግማሽ ሰዓት

ግማሽ ሰዓት ማለት ምን ማለት ነው?

ጊዜን በግማሽ ሰዓት እንዴት መግለጽ ይቻላል?

የሚከተለውን ተመልከቱ።



ጊዜ በሰዓት ሲገለጽ

የደቂቃ ጠቋሚው የሚጠቁመው 12 ላይ ነው። የሰዓት ጠቋሚው ደግሞ 8 ላይ ነው። 8 ሰዓት ነው።



ጊዜ በግማሽ ሰዓት ሲገለጽ

የደቂቃ ጠቋሚው 6 ላይ ነው። የሰዓት ጠቋሚው ደግሞ በ8 እና በ9 መካከል ነው። 8 ሰዓት ተኩል ነው።

### ምሳሌ

ቆጣሪውን ተጠቀሙ። ሰዓቱን ለዩ።

1.  9 ሰዓት ተኩል

2.  ____ ሰዓት ተኩል

3.  ____ ሰዓት ተኩል

4.  ____ ሰዓት ተኩል

5. የሒሳብ ክፍለ ጊዜ 4 ሰዓት ተኩል ላይ ይጀምራል። ተኩል ማለት ምን ማለት ነው? ተወያዩ።

## መልመጃ

ቆጣሪውን ተጠቀሙ:: ሰዓቱን ለዩ::

1. 
_____ ሰዓት **ተኩል**

2. 
_____ ሰዓት **ተኩል**

3. 
_____ ሰዓት **ተኩል**

4. 
_____ ሰዓት **ተኩል**

5. 
_____ ሰዓት **ተኩል**

6. 
_____ ሰዓት **ተኩል**

## ፕሮብሌም መፍታት

በሠንጠረዡ መሰረት ፕሮብሌሙን ፍቱ::

መልካም ከትምህርት ቤት ከተመለሰች በኋላ ጊዜዋን የምትጠቀመው ተግባሮቿን **በ1 ሰዓት ልዩነት** በመቀያየር ነው:: ሙዚቃ መጫዎት የምትጀምረው **9 ሰዓት ተኩል** ላይ ነው:: በሰንጠረዡ የተመለከቱትን ተግባሮቿን ማከናወን የምትጀምርበት ጊዜ ስንት ነው?

| ተግባር | ጊዜ |
|---|---|
| ሙዚቃ መጫዎት | |
| ማንበብ | |
| የቤት ስራ መስራት | |

**ሒሳብን በቤት:** ጊዜን በግማሽ ሰዓት ይናገሩ:: ልጆችዎ ደግሞ የሰዓት እና የደቂቃ ጠቋሚዎች የት ላይ እንደሚያርፉ እንዲገልጹ ያድርጉ::

## የሳምንቱ ቀናት

ቀን ምንድን ነው? ሳምንትስ? የጊዜ መለኪያዎች ናቸውን? በሳምንት ውስጥ ያሉት ቀናት እነማን ናቸው? የሚከተለውን ተመልከቱ::

**የመማር ውጤቶች**

- የሳምንቱ ቀናትን በቅደም ተከተል መናገር::

**ዋና ቃላት**

- ቀን ፤ ሳምንት






በሳምንት ውስጥ 7 ቀናት አሉ::



ሰኞ ከማክሰኞ በፊት ይመጣል::



ሐሙስ ከረቡዕ በኋላ ይመጣል ::

### ምሳሌ

1. የሳምንቱ ቀናት መዝሙርን ዘምሩ::

ሰኞ ፤ ማክሰኞ ፤ ረቡዕ ፤ ሐሙስ ፤ አርብ ፤ ቅዳሜ ፤ እሁድ::

ዛሬ ቀኑ ማን ነው?

ትክክለኛውን የሳምንቱ ቀን ጻፉ::

2. እሁድ የሚመጣው ከ____**ቅዳሜ**___ ቀን በኋላ ነው::

3. አርብ የሚመጣው ከ_____________ቀን በኋላ ነው::

4. ማክሰኞ የሚመጣው ከ____________ቀን በፊት ነው::

5. ሰኞ የሚመጣው ከ_____________ቀን በፊት ነው::

## መልመጃ

1. ዛሬ ቀኑ ማን ነው? ________________

2. ትናንት ቀኑ ማን ነበር? ________________

3. ነገ ቀኑ ማን ነው? ________________

4. በደብተራችሁ ከጻፋችሁ በኋላ ሰንጠረዡን አሟሉ።

| ከልደቴ ቀን በፊት | የልደቴ ቀን | ከልደቴ ቀን በኋላ |
|---|---|---|
| ረቡዕ | | |
| | ማክሰኞ | |
| | | ሐሙስ |
| ቅዳሜ | | |



የሳምንቱ ቀናት ሁልጊዜም ዙሪያ ይጓዛሉ። እሁድ በሚጠናቀቅበት ጊዜ ሰኞ እንደገና ይመጣል።

5. በሳምንቱ መጀመሪያ የሚከወነው ነገር የቱ ነው?





## ፕሮብሌም መፍታት

1. ዛሬ ቀኑ ሰኞ ነው ። ትምህርት ስለጨረስን ትምህርት ቤት ዛሬ ይዘጋል። ትምህርት ቤት እንደገና የሚከፈተው ከ7 ቀን በኋላ ነው። ትምህርት የሚከፈትበት ቀን ማን ነው?

2. ዛሬ ቀኑ አርብ ቢሆን፤ ከትናንት በፊት የነበረው ቀን የቱ ነው?

**ሒሳብን በቤት:** ልጆችዎ የሳምንቱን ቀናት በቅደም ተከተል እንዲናገሩ ያድርጉ።

# የጨዋታ ጊዜ

## ጊዜን በሰዓት እና በግማሽ ሰዓት መግለጽ



**አስፈላጊ ቁሳቁሶች:** ዳይ ፣ በኖዎች

**የጨዋታው ህግ:** ሁለት ተጫዋቾች በተራ ዳይ ከወረወሩ በኋላ የወጣው ቁጥር የወከለውን ሰዓት ቆጣሪ ይፈልጋሉ። ቆጣሪው ላይ የተገለጸውን ጊዜ ይናገራሉ። ትክክል ከሆኑ ቆጣሪውን በበኖ ይሸፍናሉ። ሁሉም ቆጣሪዎች እስከሚሸፈኑ ድረስ ይጫወታሉ። የመጨረሻዋን ቆጣሪ የሸፈነ/ች ተጫዋች አሸናፊ ነው/ናት።



## የምዕራፍ ማጠቃለያ መልመጃ

የጎደለውን ቃል አሟሉ።

1. __________ የደቂቃ ጠቋሚ ነው።   2. __________ የሰዓት ጠቋሚ ነው።

| ረጅሙ | አጭሩ |
|---|---|

ጊዜውን በሰዓት ግለጹ።

3.  __________

4.  __________

5.  __________

6.  __________

7.  __________

8.  __________

የሰዓት ቆጣሪውን በደብተራችሁ ከሳላችሁ በኋላ ጊዜውን አመልክቱ።

9. 5:00



10. 7 ሰዓት ተኩል



11. 11:30



12. ትንሽ ጊዜ የሚወስደውን ተግባር ለዩ።



 እስከ 



 እስከ 

13. ብዙ ጊዜ የሚወስደውን ተግባር ለዩ፡፡







---

14. የሰዓት ቆጣሪው በ4 እና በ5 መካከል ላይ አርፏል፡፡

ደቂቃ ቆጣሪው ደግሞ 6 ላይ አርፏል፡፡

ስንት ሰዓት ሆነ?



---

15. የሳይንስ እና ቴክኖሎጂ የክበብ ውይይት የሚጀምረው 9 ሰዓት ላይ ነው፡፡

ከ1 ሰዓት የፕሮጀክት ስራ በኋላ ይጠናቀቃል፡፡

ውይይቱ ስንት ሰዓት ላይ ይጠናቀቃል? ________ሰዓት

---

በሠንጠረዡ መሰረት ፕሮብሌሙን ፍቱ፡፡

16. ከባህር ዳር ከተማ ገበያ አካባቢ የሚነሱ አውቶቡሶች ተራቸውን ጠብቀው **በግማሽ ሰዓት** ልዩነት ወደ አባይ ማዶ አካባቢ ይሄዳሉ፡፡ የመጀመሪያው አውቶቡስ የሚነሳው **1 ሰዓት ተኩል** ላይ ነው፡፡

2ኛው፣ 3ኛው እና 4ኛው አውቶቡስ የሚነሱበት ጊዜ ስንት ነው?

| የአውቶቡስ ቁጥር | የሚነሱበት ጊዜ |
|---|---|
| 1 | 1 ሰዓት ተኩል |
| 2 | |
| 3 | |
| 4 | |

---

# ምዕራፍ 6 እስከ 100 ያሉ ቁጥሮች



በምስሉ ላይ የሚታዩት ጢንዚዛዎች ምን ያክል ይሆናሉ? እንዴት ማወቅ ይቻላል?

## የቀደመ እውቀታችሁን ከልሱ

1. የጎደሉትን ቁጥሮች አሟሉ።

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | | 3 | | 5 | | 7 |
| 8 | | 10 | | 12 | | 14 |
| 15 | | 17 | 18 | | | |

ቁጠሩ። ቁጥሩን በደብተራችሁ ጻፉ።

2.  ______ ኮፍያዎች

3.  ______ ቦኖዎች

4. የሁሴን ቤተሰቦች 3 ካርቶን ደብተር ለልጆቻቸው መማሪያ ገዙ። በእያንዳንዱ ካርቶን ውስጥ 10 ደብተሮች አሉ። በአጠቃላይ ስንት ደብተሮችን ገዙ? _________ ደብተሮች

## በአስር መቁጠር

**የመማር ውጤቶች**
- አስሮችን መቁጠር እና መጻፍ::

**ዋና ቃላት**
- አንዶች
- አስሮች

ነገሮችን አንድ በአንድ መቁጠር ይቻላልን?

አስር በአስር መቁጠር ይቻላልን?

የሚከተለውን ተመልከቱ::



10 አንዶች          1 አስር = 10

እነዚህ ኩቦች በአንድ ሲቆጠሩ 10 አንዶች ይሆናሉ:: በአንድ ላይ ሲታሰሩ ደግሞ 1 አስር ይሆናሉ::



20 አንዶች          2 አስሮች = 20

ስለዚህ ስንት ነገሮች እንዳሉ ለማወቅ በ10 መቁጠር ይቻላል::
10፣ 20፣ 30፣ 40፣ 50

### ምሳሌ

አስሮችን ቁጠሩ:: ለመቁጠር ኩቦችን  ተጠቀሙ:: ቁጥሩን በደብተራችሁ ጻፉ::

**1.**



__3__ አስሮች = __30__ ሠላሳ

**2.**



______ አስሮች = ______ ሥልሳ

**3.**



______ አስሮች = ______ ሰማንያ

**4.**



______ አስሮች = ______ አርባ

**5.** 100 ቁጥርን ለማሳየት ኩቦችን እንዴት መጠቀም ይቻላል? ተወያዩ::

## መልመጃ

አስሮችን ቁጠሩ። ኩቦችን ተጠቀሙ። ቁጥሩን በደብተራችሁ ጻፉ።

1. 

______ አስሮች = ______
ሠባ

2. 

______ አስሮች = ______
አምሳ

3. 

______ አስሮች = ______
ዘጠና

4. 

______ አስር = ______
አስር

ቁጥሩን በደብተራችሁ ጻፉ።

5. 7 አስሮች = ______
6. 4 አስሮች = ______
7. 3 አስሮች = ______

## ፕሮብሌም መፍታት

1. ሸዋየ እስከ 100 ያሉ ቁጥሮችን በአስር እየቆጠረች ነበር። ከ10 ጀምራ በመቁጠር በደብተሯ ላይ 7 ቁጥሮችን ጻፈች። ሸዋየ በመጨረሻ የጻፈችው ቁጥር ስንት ነበር?

2. የወላጆች ቀን ክብረ በዓል ወቅት 10 ወንበሮች በአግድም ተደረደሩ።
   በ4 አግድም ስንት ወንበሮችን መደርደር ይቻላል? ________ ወንበሮች

3. ሳሚያ መጽሐፍ ማንበብ ስለምትወድ ቤተሰቦቿ የገዙላት ብዙ መጽሐፍት አሏት። መጽሐፍቶቿን ለመቁጠር በአስር አቧደነቻቸው። 3 የአስር ቡድኖች ቢኖሯት ስንት መጽሐፍት አሏት? __________ መጽሐፍት

**ሒሳብን በቤት:** ልጆችዎ የቤተሰቡን የጣት ብዛት እንዲፈልጉ ያድርጉ። መልሱን ለማግኘት በአስር መቁጠር እንዴት እንደሚችሉ ይጠይቁ።

# ቁጥሮችን በአስሮች መገመት

**የመማር ውጤቶች**

- አስሮችን በመጠቀም የነገሮችን ብዛት መገመት::

**ዋና ቃል**

- መገመት

የነገሮችን ብዛት በተናጠል ሳንቆጥር መገመት ትችላላችሁን? ምን ዓይነት መንገድ መከተል ይቻላል? የሚከተለውን ተመልከቱ::



የብዮች ብዛት ወደ ስንት ይጠጋል?

በመገመት: 30 በመቁጠር: 31

መጀመሪያ 10 ብዮችን ለዩ:: ከዚያም ጠቅላላ ቁጥሩን ገምቱ:: በመጨረሻም ትክክለኛ ቁጥሩን ለማወቅ እያንዳንዱን ቁጠሩ::

## ምሳሌ

አንድ የአስር ቡድን ለዩ:: ጠቅላላ ቁጥሩን ገምቱ:: ከዚያም እያንዳንዱን በመቁጠር አረጋግጡ::

1. 

በመገመት: 40 በመቁጠር: 42

2. 

በመገመት: ____ በመቁጠር: ____

3. 

በመገመት: ____ በመቁጠር:

4. 

በመገመት: ____ በመቁጠር: ____

5. የአስር ቡድን መለየት ለመገመት እንዴት ሊያግዛችሁ ቻለ? ተወያዩ::

## መልመጃ

አንድ የአስር ቡድን ለዩ። ቁጥሩን ገምቱ። ከዚያም እያንዳንዱን በመቁጠር አረጋግጡ።

1. 

በመገመት: ____ በመቁጠር: ____

2. 

በመገመት: ____ በመቁጠር: ____

3. 

በመገመት: ____ በመቁጠር: ____

4. 

በመገመት: ____ በመቁጠር: ____

## ፕሮብሌም መፍታት

1. ብዛታቸው ወደ 70 የሚጠጉ የአበባ ስዕሎች እንዳሏት ነጻነት ለጓደኞቿ ነገረቻቸው። ከሚከተሉት መካከል የትኛው ቁጥር ነጻነት ያሏትን የአበባ ስዕሎች ብዛት ያሳያል?

   27 57 72 97

2. የከፍያለው እናት ለልጆቿ መማርያ የሚሆን 10 ካርቶን ደብተር ገዝታለች። እያንዳንዱ ካርቶን 10 ደብተር ይዟል። የከፍያለው እናት በአመቱ መጨረሻ 8 ደብተር ይቀራታል። ምን ያክል ደብተር ለልጆቿ እንደሰጠቻቸው ለማወቅ የተሻለ ግመታ የሚሆነው 10 ነው ወይንስ 90? አብራሩ።

**ሒሳብን በቤት:** ለልጆችዎ በእጅ መዳፍ ሙሉ ጥራጥሬ (ለምሳሌ ባቄላ) ይስጡ። ቁጥራቸውን እንዲገምቱ ያድርጉ። ከዚያም ትክክለኛ ቁጥሩን ለማወቅ እንዲቆጥሩ ያድርጉ።

# እስከ 100 ያሉ ቁጥሮችን በአንድ መቁጠር

**የመማር ውጤቶች**

- የቁጥር ሠንጠረዥን በመጠቀም እስከ 100 ያሉ ቁጥሮችን በቅደም ተከተል መቁጠር እና መጻፍ።

**ዋና ቃላት**

- የቁጥር ሠንጠረዥ

የቁጥሮችን ቅደም ተከተል በመጠቀም እስከ 100 ያሉ ቁጥሮችን መቁጠር ይቻላልን?

የሚከተለውን የቁጥር ሠንጠረዥ ተመልከቱ።

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 |
| 11 | 12 | 13 | 14 | 15 | 16 | 17 | 18 | 19 | 20 |
| 21 | 22 | 23 | 24 | 25 | 26 | 27 | 28 | 29 | 30 |
| 31 | 32 | 33 | 34 | 35 | 36 | 37 | 38 | 39 | 40 |
| 41 | 42 | 43 | 44 | 45 | 46 | 47 | 48 | 49 | 50 |
| 51 | 52 | 53 | 54 | 55 | 56 | 57 | 58 | 59 | 60 |
| 61 | 62 | 63 | 64 | 65 | 66 | 67 | 68 | 69 | 70 |
| 71 | 72 | 73 | 74 | 75 | 76 | 77 | 78 | 79 | 80 |
| 81 | 82 | 83 | 84 | 85 | 86 | 87 | 88 | 89 | 90 |
| 91 | 92 | 93 | 94 | 95 | 96 | 97 | 98 | 99 | 100 |

ከ41 መቁጠር ብትጀምሩ ቀጣይ የምትጠሩት ቁጥር ስንት ነው? 42 ነውን?

የቁጥር ሠንጠረዥ ቁጥሮችን በቅደም ተከተል ለመቁጠር

## ምሳሌ

የቁጥር ሠንጠረዥን በደብተራችሁ ጻፉ።

1. ከ1 እስከ 30 ቁጠሩ። በአረንጓዴ ቀለም ቀቡ።
2. ከ31 እስከ 70 ቁጠሩ። በቢጫ ቀለም ቀቡ።
3. ከ71 እስከ 100 ቁጠሩ። በቀይ ቀለም ቀቡ።

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 |
| 11 | 12 | 13 | 14 | 15 | 16 | 17 | 18 | 19 | 20 |
| 21 | 22 | 23 | 24 | 25 | 26 | 27 | 28 | 29 | 30 |
| 31 | 32 | 33 | 34 | 35 | 36 | 37 | 38 | 39 | 40 |
| 41 | 42 | 43 | 44 | 45 | 46 | 47 | 48 | 49 | 50 |
| 51 | 52 | 53 | 54 | 55 | 56 | 57 | 58 | 59 | 60 |
| 61 | 62 | 63 | 64 | 65 | 66 | 67 | 68 | 69 | 70 |
| 71 | 72 | 73 | 74 | 75 | 76 | 77 | 78 | 79 | 80 |
| 81 | 82 | 83 | 84 | 85 | 86 | 87 | 88 | 89 | 90 |
| 91 | 92 | 93 | 94 | 95 | 96 | 97 | 98 | 99 | 100 |

የቁጥር ሠንጠረዥ በመጠቀም ቁጥሮችን በቅደም ተከተል ጻፉ።

4. 23 31 13 13 23 31
5. 35 27 20 ___ ___ ___
6. 85 68 59 74 _____ _____ _____ _____
7. 52 36 48 65 _____ _____ _____ _____
8. በቁጥር ሠንጠረዥ ላይ ከ20 የሚያንሱ ቁጥሮች ስንት ናቸው? ተወያዩ።

## መልመጃ

1. በደብተራችሁ ከጻፋችሁ በኋላ የጎደሉትን ቁጥሮች አሟሉ።

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 |
| 11 | 12 | 13 | 14 | 15 | 16 | 17 | 18 | 19 | 20 |
| | | | | | | | | | |
| 31 | 32 | 33 | 34 | 35 | 36 | 37 | 38 | 39 | 40 |
| 41 | 42 | 43 | 44 | 45 | | | | | |
| | | | | | 56 | 57 | 58 | 59 | 60 |
| 61 | 62 | 63 | 64 | 65 | | | | | |
| | 72 | 73 | 74 | 75 | 76 | 77 | 78 | 79 | 80 |
| 81 | 82 | 83 | 84 | 85 | 86 | 87 | 88 | 89 | 90 |
| | | | | | | | 98 | 99 | 100 |

**አስተውሉ**

በቁጥር ሰንጠረዥ ላይ ቁጥሮች የተቀመጡት በቅደም ተከተል ነው።

የቁጥር ሠንጠረዥ በመጠቀም ቁጥሮችን በቅደም ተከተል ጻፉ።

2. 44 14 41 ____ ____ ____

3. 89 81 18 ____ ____ ____

4. 38 29 47 ____ ____ ____

5. 74 8 49 ____ ____ ____

6. 22 14 87 78 ____ ____ ____

7. 18 96 37 3 ____ ____ ____ ____

## ፕሮብሌም መፍታት

ስለ ቁጥር ሰንጠረዥ የምታውቁትን ተጠቅማችሁ ባዶ ሳጥኖችን በደብተራችሁ በመጻፍ አሟሉ።

1.




2.




**ሒሳብን በቤት:** ልጆችዎ ከቁጥር ሠንጠረዥ ላይ አንድ ቁጥር እንዲመርጡ ያድርጉ። ከዚያ ቁጥር በመነሳት ወደ ኋላ እስከ 1 ወደፊት ደግሞ እስከ 100 እንዲቆጥሩ ያድርጉ።

## እያለፉ መቁጠር

የቁጥር ሰንጠረዥን በመጠቀም እያለፉ መቁጠር ይቻላልን? ከዚህ በታች ያለውን ተመልከቱ::

በስንት እያለፉ መቁጠርን ያሳያል?

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | | 3 | | 5 | | 7 | | 9 | |
| 11 | | 13 | | 15 | | 17 | | 19 | |
| 21 | | 23 | | 25 | | 27 | | 29 | |
| 31 | | 33 | | 35 | | 37 | | 39 | |
| 41 | | 43 | | 45 | | 47 | | 49 | |
| 51 | | 53 | | 55 | | 57 | | 59 | |
| 61 | | 63 | | 65 | | 67 | | 69 | |
| 71 | | 73 | | 75 | | 77 | | 79 | |
| 81 | | 83 | | 85 | | 87 | | 89 | |
| 91 | | 93 | | 95 | | 97 | | 99 | |

በ2 እያለፉ መቁጠርን ያሳያል::

**የመማር ውጤቶች**

- በቁጥር ሠንጠረዥ ላይ በ2፣ በ5 እና በ10 እያለፉ መቁጠር::

**ዋና ቃላት**

- እያለፉ መቁጠር

### ምሳሌ

ከላይ የተሰጠውን የቁጥር ሰንጠረዥ በደብተራችሁ በመጻፍ መልሱ::

1. በ2 ቁጠሩ:: የታለፉትን ቁጥሮች ጻፉ::
2. በ5 ቁጠሩ:: ቁጥሮችን ቀይ ቀለም ቀቡ::
3. በ10 ቁጠሩ:: ቁጥሮችን አረንጓዴ ቀለም ቀቡ::

በተሰጠው መሰረት በመቁጠር ባዶ ቦታዎችን አሟሉ:: በደብተራችሁ ጻፉ::

4. 8፣ 10፣ 12፣ 14፣ _____፣ _____፣ _____፣ _____፣ _____፣ _____::
5. 25፣ 30፣ 35፣ 40፣ _____፣ _____፣ _____፣ _____፣ _____::
6. 40፣ 50፣ 60፣ _____፣ _____፣ _____፣ _____::
7. በ2፣ በ5 ወይንም በ10 እያለፋችሁ ስትቆጥሩ ከየት ጀመራችሁ? ለምን? ተወያዩ::

## መልመጃ

የቁጥር ሰንጠረዥን በደብተራችሁ ላይ በመጻፍ ጥያቄዎችን መልሱ።

1. በ5 ቁጠሩ። ቁጥሮችን አክብቡ።

2. በ10 ቁጠሩ። በቁጥሮች ላይ የX ምልክት አድርጉ።

3. በ2 ቁጠሩ። ቁጥሮችን ሰማያዊ ቀለም ቀቡ።

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 |
| 11 | 12 | 13 | 14 | 15 | 16 | 17 | 18 | 19 | 20 |
| 21 | 22 | 23 | 24 | 25 | 26 | 27 | 28 | 29 | 30 |
| 31 | 32 | 33 | 34 | 35 | 36 | 37 | 38 | 39 | 40 |
| 41 | 42 | 43 | 44 | 45 | 46 | 47 | 48 | 49 | 50 |
| 51 | 52 | 53 | 54 | 55 | 56 | 57 | 58 | 59 | 60 |
| 61 | 62 | 63 | 64 | 65 | 66 | 67 | 68 | 69 | 70 |
| 71 | 72 | 73 | 74 | 75 | 76 | 77 | 78 | 79 | 80 |
| 81 | 82 | 83 | 84 | 85 | 86 | 87 | 88 | 89 | 90 |
| 91 | 92 | 93 | 94 | 95 | 96 | 97 | 98 | 99 | 100 |

በተሰጠው መሰረት ባዶ ቦታዎችን አሟሉ።

4. 55፣ 50፣ 65፣ 70፣ _____፣ _____፣ _____፣ _____፣ _____፣ _____።

5. 82፣ 84፣ 86፣ 88፣ _____፣ _____፣ _____፣ _____፣ _____፣ _____።

6. 100፣ 90፣ 80፣ 70፣ 60፣ _____፣ _____፣ _____፣ _____፣ _____።

## ፕሮብሌም መፍታት

1. ከትምህርት ቤታችን አጥር ላይ 6 ወፎች ተቀምጠዋል። ከአጥሩ ላይ ስንት የወፍ እግሮች አሉ? _______ እግሮች

2. የሒሳብ መምህር የክፍሉ ተማሪዎችን በ8 ቡድኖች መደቧቸው። እያንዳንዱ ቡድን 5 ተማሪዎችን ይዟል። በአጠቃላይ በክፍሉ ውስጥ ስንት ተማሪዎች አሉ?

3. ማክዳ በሚከተለው መልክ በ10 እያለፈች ቆጠረች። ማክዳ ትክክል ሰርታለችን? ስህተት ከሰራች አስተካክላችሁ ጻፉ።




**ሒሳብን በቤት:** ልጆችዎ እያለፉ የሚቆጠሩ ነገሮችን (ለምሳሌ ጫማዎች፣ የእጅ እና እግር ጣቶች) እንዲፈልጉ ያድርጉ። ከዚያም እያለፉ በመቁጠር ስንት እንደሆኑ እንዲናገሩ ያድርጉ።

## ቁጥሮችን በአስሮች እና በአንዶች መጻፍ

**የመማር ውጤቶች**

- ቁጥሮችን በአስሮች እና በአንዶች መጻፍ።

**ዋና ቃል**

- ሆሄ

10 አንዶችን በማጣመር 1 አስር ማድረግ እንደሚቻል ተገንዝባቹኂል። አንድ ቁጥርን በአስሮች እና በአንዶች እንዴት መጻፍ እንደሚቻልስ ታውቃላችሁ?

የሚከተለውን ተመልከቱ።

14 ባለሁለት **ሆሄ** ቁጥር ነው።

በ14 ላይ 1 የሚያመለክተው ምንን ነው? 1 አስር እንዳለ ያሳያል።

በ14 ላይ 4 ደግሞ የሚያመለክተው 4 አንዶችን ነው።

 = 

14 አንዶች = 1 አስር እና 4 አንዶች

14 = 10 + 4

**አስተውሉ**

10 አንዶች እና 4 አንዶች ከ1 አስር እና 4 አንዶች ጋር ተመሳሳይ ነው።

### ምሳሌ

ኩቦችን ተጠቀሙ። ስንት አስሮች እና ስንት አንዶች እንዳሉ ግለጹ። ቁጥሩን በደብተራችሁ ጻፉ።

1. 
12 አንዶች = __1__አስር እና __2__አንዶች።
__10__ + __2__ = __12__

2. 
18 አንዶች = ______አስር እና ______አንዶች።
______ + ______ = ______

3. 26 አንዶች = _____አስሮች እና _____አንዶች። _____ + _____ = _____
4. 52 አንዶች = _____አስሮች እና _____አንዶች። _____ + _____ = _____
5. 20 አንዶችን እንዴት በአስሮች እና በአንዶች መግለጽ ይቻላል? ተወያዩ።

## መልመጃ

ኩቦችን  ተጠቀሙ:: ስንት አስሮች እና ስንት አንዶች እንዳሉ ግለጹ:: ቁጥሩን በደብተራችሁ ጻፉ::

1. 

13 አንዶች = _____ አስር እና _____ አንዶች::

_____ + _____ = _____

2. 

22 አንዶች = ___ አስሮች እና ___ አንዶች::

____ + ____ = ____

3. 

19 አንዶች = ___ አስር እና ___ አንዶች::

____ + ____ = ____

4. 31 አንዶች = _____ አስሮች እና _____ አንድ:: _____ + _____ = _____

5. 42 አንዶች = _____ አስሮች እና _____ አንዶች:: _____ + _____ = _____

6. 65 አንዶች = _____ አስሮች እና _____ አንዶች:: _____ + _____ = _____

## ፕሮብሌም መፍታት

1. መኮነን 25 እርሳሶች አሉት:: ከቦርሳው ላይ ባሉት 3 ኪሶች ማስቀመጥ ፈለገ:: እያንዳንዱ ኪስ ሊይዝ የሚችለው የእርሳስ ብዛት 10 ብቻ ነው:: መኮነን በእያንዳንዱ ኪስ ስንት እርሳሶችን ማስቀመጥ ይችላል? _____ + _____ + _____ = _____

2. ሐዋ 30 ፊኛዎች ነበሯት:: ለራሔል፣ ለሒክማ እና ለዳዊት እኩል ቁጥር ያላቸው ፊኛዎችን መስጠት ፈለገች:: ለእያንዳንዳቸው ስንት ፊኛዎችን ሰጠች?

3. ቅዱስ 37 እርሳሶች አሉት:: በአስር ቢያቧድናቸው ምን ያክል አስሮች ይኖሩታል? በቡድኑ ውስጥ ያልገቡ ምን ያክል እርሳሶች ይኖሩታል?

**ሒሳብን በቤት:** ልጆችዎ 78 አንዶችን በአስሮች እና በአንዶች እንዲገልጹ ያድርጉ::

# የቁጥር ቤት ዋጋ

**የመማር ውጤቶች**
- የባለ ሁለት ሆሄ ቁጥሮችን የቤት ዋጋ መለየት፡፡
- እስከ 100 ያሉ ቁጥሮችን ማንበብ እና መጻፍ፡፡

**ዋና ቃላት**
- ባለ ሁለት ሆሄ ቁጥር
- የቁጥር ቤት ዋጋ

የቁጥር ሆሄ ታውቃላችሁን?

ባለሁለት ሆሄ ቁጥር እንዴት ይገለጻል?

የባለሁለት ሆሄ ቁጥር የእያንዳንዱን ሆሄ ዋጋ እንዴት ማወቅ ይቻላል?

የሚከተለውን ተመልከቱ፡፡



24

| የ10 ቤት | የ1 ቤት |
|---|---|
| 2 | 4 |

2 አስሮች እና 4 አንዶች

ሆሄ 2 በአስር ቤት ትገኛለች፡፡ ይህም 2 አስሮች ወይንም 20 እንዳሉ ያሳያል፡፡

ሆሄ 4 ደግሞ በአንድ ቤት ትገኛለች፡፡ ይህም 4 አንዶች እንዳሉ ያሳያል፡፡

በተጨማሪ የሚከተሉትን ባለ ሁለት ሆሄ ቁጥሮች ተመልከቱ፡፡

| የ10 ቤት | የ1 ቤት |
|---|---|
|  |  |

3 አስሮች እና 4 አንዶች = 34

በ34 ውስጥ ሆሄ 3 የሚያሳየው 3 አስሮችን፣ ወይም 30ን ነው፡፡

| የ10 ቤት | የ1 ቤት |
|---|---|
|  |  |

4 አስሮች እና 3 አንዶች = 43

በ43 ውስጥ ግን ሆሄ 3 የሚሳየው 3 አንዶችን፣ ወይም 3ን ነው፡፡

**ማስታወሻ**

0 ፣ 1 ፣ 2 ፣ 3 ፣ 4 ፣ 5 ፣ 6 ፣ 7 ፣ 8 እና 9 **የቁጥር ሆሄ** ይባላሉ፡፡

ሆሄዎች የተቀመጡበትን ቦታ ወይንም ቤት በመለየት የቁጥርን ሆሄ **የቤት ዋጋ** ማወቅ ይቻላል፡፡

## ምሳሌ

በቀይ የተቀለመውን የቁጥር ሆሄ ዋጋ ለዩ፡፡

1. 27



70 (7)

2. 46



40 4

3. 30



30 3

4. 56



60 6

5. 71



10 1

6. 25



20 2

ኩቦችን  ፣  በመጠቀም አስሮችን እና አንዶችን አሳዩ፡፡ ቁጥሩን በደብተራችሁ ጻፉ፡፡

7.

| የ10 ቤት | የ1 ቤት |
|---|---|
|  |  |

| የ10 ቤት | የ1 ቤት |
|---|---|
| 1 | 3 |

1 አስር 3 አንዶች = 13

አስራ ሦስት

8.

| የ10 ቤት | የ1 ቤት |
|---|---|
|  |  |

| የ10 ቤት | የ1 ቤት |
|---|---|
| 3 | 5 |

___ አስሮች ___ አንዶች = ____

ሠላሳ አምስት

9.

| የ10 ቤት | የ1 ቤት |
|---|---|
|  |  |

| የ10 ቤት | የ1 ቤት |
|---|---|
| 4 | 6 |

____ አስሮች ____ አንዶች = _____

አርባ ስድስት

10.

| የ10 ቤት | የ1 ቤት |
|---|---|
|  |  |

| የ10 ቤት | የ1 ቤት |
|---|---|
| 2 | 4 |

____ አስሮች ____ አንዶች = ____

ሃያ አራት

11. 25 እና 52 እንዴት ይለያያሉ? እንዴትስ ይመሳሰላሉ? ተወያዩ፡፡

## መልመጃ

በቀይ የተቀለመውን የቁጥር ሆሄ ዋጋ ለዩ፡፡

1. 17



10   1

2. 32



20   2

3. 43



40   4

4. 28



80   8

5. 65



60   6

6. 59



90   9

ኩቦችን  ፣  በመጠቀም አስሮችን እና አንዶችን ለዩ፡፡
ቁጥሩን በደብተራችሁ ጻፉ፡፡

7.

| የ10 ቤት | የ1 ቤት |
|---|---|
|  |  |

| የ10 ቤት | የ1 ቤት |
|---|---|
| 4 | 3 |

___ አስሮች ___ አንዶች =_____
አርባ ሦስት

8.

| የ10 ቤት | የ1 ቤት |
|---|---|
|  |  |

| የ10 ቤት | የ1 ቤት |
|---|---|
| 2 | 9 |

___ አስሮች ___ አንዶች =_____
ሃያ ዘጠኝ

9.

| የ10 ቤት | የ1 ቤት |
|---|---|
|  |  |

| የ10 ቤት | የ1 ቤት |
|---|---|
| 5 | 8 |

___ አስሮች ___ አንዶች =_____
አምሳ ስምንት

10.

| የ10 ቤት | የ1 ቤት |
|---|---|
|  |  |

| የ10 ቤት | የ1 ቤት |
|---|---|
| 6 | 4 |

___ አስሮች ___ አንዶች =_____
ስልሳ አራት

## ፕሮብሌም መፍታት

1. አዝራሮችን በአስር አቧድኑ፡፡



ሀ. ስንት አስሮች ሆኑ? _______ አስሮች

ለ. ስንት አንዶች ቀሩ? ________ አንዶች

ሐ. በአጠቃላይ ስንት አዝራሮች አሉ? _________ አዝራሮች

2. የተገለጸውን እውነታ የሚያሟላ ባለሁለት ሆሄ ቁጥር ፈልጉ፡፡

ሀ. የእኔ ቁጥር 8 አስሮች አሉት፡፡ በ1 ቤት ያለው ሆሄ በ10 ቤት ካለው ሆሄ ይበልጣል፡፡ የእኔ ቁጥር ስንት ነው፡፡

ለ. በእኔ ቁጥር ውስጥ በ1 ቤት ያለው ሆሄ በ10 ቤት ያለውን ሆሄ እጥፍ ነው፡፡ ሆሄዎቹ ሲደመሩ 3 ይሆናል፡፡ የኔ ቁጥር ስንት ነው፡፡

3. ምስሎች የሚያሳዩትን ቁጥር በደብተራችሁ ጻፉ፡፡

ከ50 እስከ 70 የሚደርሱ ቁጥሮችን የሚያሳየውን ለዩ፡፡

ሀ.



__________

ለ.



__________

ሐ.



__________

**ሒሳብን በቤት:** ለልጆችዎ በዛ ያሉ ነገሮችን (ለምሳሌ እስከ 50 የሚደርሱ ጠጠሮችን ወይም ጥራጥሬ) ይስጡ፡፡ ልጆችዎ በአስሮች እና በአንዶች በማቧደን እንዲመድቡ ያድርጉ፡፡ ከዚያም ቁጥሩን እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡

## እስከ 100 ያሉ ቁጥሮችን ማወዳደር

**የመማር ውጤቶች**
- እስከ 100 ያሉ ቁጥሮችን ማወዳደር፡፡

**ዋና ቃላት**
- ይበልጣል፣ ያንሳል፣

አንድ ባለሁለት ሆሄ ቁጥር ከሌላኛው ቁጥር እንደሚበልጥ፣ እንደሚያንስ ወይም እኩል እንደሚሆን እንዴት ማወቅ ይቻላል? የሚከተለውን ተመልከቱ፡፡

3 አስሮች ከ2 አስሮች ይበልጣሉ፡፡



34 **ይበልጣል** ከ24

34 > 24

4 አንዶች ከ6 አንዶች ያንሳሉ፡፡



24 **ያንሳል** ከ26

24 < 26

አንዶችም አስሮችም እኩል ናቸው፡፡



24 **እኩል ይሆናል** ከ24

24 = 24

ባለሁለት ሆሄ ቁጥሮችን ለማወዳደር የምንጠቀምበትን መንገድ ለያችሁ?
መጀመሪያ አስሮችን ማወዳደር፡፡
አስሮች ተመሳሳይ ከሆኑ ደግሞ አንዶችን ማወዳደር፡፡

### ምሳሌ

ለማወዳደር ኩቦችን ተጠቀሙ፡፡ ሠንጠረዡን በደብተራችሁ ጻፉ፡፡

| | የሚበልጠውን ቁጥር አክብቡ፡፡ | ለመወሰን ያገዛችሁን ለዩ ፡፡ | ቁጥሮችን ጻፉ፡፡ |
|---|---|---|---|
| 1. | 62 (65) | አስሮች (አንዶች) | 65 ይበልጣል ከ62፡፡<br>65 > 62 |
| 2. | 84 48 | አስሮች አንዶች | _____ ይበልጣል ከ_____፡፡<br>_____ > _____ |
| 3. | 72 70 | አስሮች አንዶች | _____ ይበልጣል ከ_____፡፡<br>_____ > _____ |

| | የሚያንሰውን ቁጥር አክብቡ:: | ለመወሰን ያገዛችሁን ለዩ :: | ቁጥሮችን ጻፉ:: |
|---|---|---|---|
| 4. | 93 (80) | (አስሮች) አንዶች | 80 ያንሳል ከ93::<br>80 < 93 |
| 5. | 39 36 | አስሮች አንዶች | _____ ያንሳል ከ_____::<br>_____ < _____ |
| 6. | 57 47 | አስሮች አንዶች | _____ ያንሳል ከ_____::<br>_____ < _____ |

የ>፣ < ወይም = ምልክቶችን በመጠቀም አወዳድሩ:: በደብተራችሁ አሳዩ::

| | | |
|---|---|---|
| 7. 27 ◯ 15 | 8. 100 ◯ 100 | 9. 47 ◯ 74 |
| 10. 60 ◯ 59 | 11. 63 ◯ 36 | 12. 51 ◯ 48 |

13. 67 ከ77 እንደሚያንስ እንዴት አወቃችሁ? ተወያዩ::

ይበልጣል >
ያንሳል <
እኩል ይሆናል =

**መልመጃ**

ሠንጠረዡን በደብተራችሁ ጻፉ:: ለማወዳደር ኩቦችን ተጠቀሙ::

| | የሚበልጠውን ቁጥር አክብቡ:: | ለመወሰን ያገዛችሁን ለዩ :: | ቁጥሮችን ጻፉ:: |
|---|---|---|---|
| 1. | 65 55 | አስሮች አንዶች | _____ ይበልጣል ከ_____::<br>_____ > _____ |
| 2. | 94 98 | አስሮች አንዶች | _____ ይበልጣል ከ_____::<br>_____ > _____ |
| 3. | 57 75 | አስሮች አንዶች | _____ ይበልጣል ከ_____::<br>_____ > _____ |

| | የሚበልጠውን ቁጥር አክብቡ፡፡ | ለመወሰን ያገዛችሁን ለዩ ፡፡ | ቁጥሮችን ጻፉ፡፡ |
|---|---|---|---|
| 4. | 47 48 | አስሮች አንዶች | _____ ያንሳል ከ_____፡፡<br>_____ < _____ |
| 5. | 82 28 | አስሮች አንዶች | _____ ያንሳል ከ_____፡፡<br>_____ < _____ |
| 6. | 96 90 | አስሮች አንዶች | _____ ያንሳል ከ_____፡፡<br>_____ < _____ |

የ > ፣ < ፣ ወይንም = ምልክቶችን በመጠቀም አወዳድሩ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| 7. 64 ◯ 23 | 8. 37 ◯ 50 | 9. 43 ◯ 43 |
| 10. 87 ◯ 78 | 11. 100 ◯ 10 | 12. 56 ◯ 63 |

## ፕሮብሌም መፍታት

1. ከ27 የሚያንሱ ብዮች አሉኝ፡፡ ከ23 ግን ይበልጣሉ፡፡ ምን ያክል ብዮች ሊኖሩኝ ይችላሉ? እንዴት አወቃችሁ?

2. ተስፋሁን እና ሃይማኖት ነጥብ የሚያስገኝ የካርድ ጨዋታ እየተጫወቱ ነው፡፡ ተስፋሁን ያገኘው ነጥብ 2 አስሮች እና 8 አንዶች አሉት፡፡ የሃይማኖት ነጥብ ደግሞ 2 አንዶች እና 8 አስሮች አሉት፡፡ በጨዋታው የበለጠ ነጥብ ያገኘው ማን ነው?

3. አደም የሚከተሉት የቁጥር ካርዶች ነበሩት፡፡ ከ49 የሚያንሱ እና ከ53 የሚበልጡ ቁጥሮች የተጻፉባቸውን ካርዶች ለጓደኞቹ ሰጣቸው፡፡ የትኞቹ የቁጥር ካርዶች ቀሩት?

47 48 51 52 54

**ሒሳብን በቤት:** ባለ ሁለት ሆሄ ቁጥር ይጻፉ፡፡ ልጆችዎ ከተሰጠው ቁጥር የሚያንሱ ሁለት ቁጥሮችን፣ የሚበልጡ ደግሞ ሁለት ቁጥሮችን እንዲናገሩ እና እንዲጽፉ ያድርጉ፡፡

# እስከ 100 ያሉ ቁጥሮችን በቅደም ተከተል ማስቀመጥ

**የመማር ውጤቶች**

- እስከ 100 ያሉ ቁጥሮችን በቅደም ተከተል ማስቀመጥ፡፡

የቁጥር መስመር ታውቃላችሁ፡፡

ቁጥሮችን በቅደም ተከተል ለማስቀመጥ ይረዳል፡፡

የሚከተለውን ተመልከቱ፡፡




23 ከ24 ቀድሞ ይገኛል፡፡ 23 ከ24 **በፊት** ይገኛል ማለት ነው፡፡

29 ከ28 ተከትሎ ይገኛል፡፡ 29 ከ28 **በኋላ** ይገኛል ማለት ነው፡፡

26 ደግሞ በ25 እና በ27 **መካከል** ይገኛል፡፡

23 ከ24 በአንድ ያንሳል፡፡

29 ከ28 በአንድ ይበልጣል፡፡

**ምሳሌ**




**በፊት** የሚገኘውን ቁጥር በደብተራችሁ ጻፉ፡፡ የቁጥር መስመሩን ተጠቀሙ፡፡

1. 27 ፣ 28 | 2. _____ ፣ 32 | 3. _____ ፣ 25

**በኋላ** የሚገኘውን ቁጥር ለዩ

4. 20 ፣ _____ | 5. 33 ፣ _____ | 6. 23 ፣ _____

**መካከል** ላይ የሚገኘውን ቁጥር ለዩ

7. 33 ፣ _____ ፣ 35 | 8. 21 ፣ _____ ፣ 23 | 9. 29 ፣ _____ ፣ 31

ቁጥሮችን በቅደም ተከተል አስቀምጡ፡፡

10. 91 89 92
_____ _____ _____

11. 59 56 58 57
_____ _____ _____ _____

12. 30 32 33 31 _____ _____ _____ _____

## መልመጃ

60 61 62 63 64 65 66 67 68 69 70 71 72 73 74 75

**በፊት** የሚገኘውን ቁጥር በደብተራችሁ ጻፉ፡፡ የቁጥር መስመሩን ተጠቀሙ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| 1. ____ ፣ 68 | 2. _____ ፣ 75 | 3. _____ ፣ 62 |

**በኋላ** የሚገኘውን ቁጥር ለዩ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| 4. 75 ፣ ______ | 5. 60 ፣ ______ | 6. 66 ፣ ______ |

**መካከል** ላይ የሚገኘውን ቁጥር ለዩ

| | | |
|---|---|---|
| 7. 63 ፣ _____ ፣ 65 | 8. 71 ፣ _____ ፣ 73 | 9. 67 ፣ ____ ፣ 69 |

ቁጥሮችን በቅደም ተከተል አስቀምጡ፡፡

| | |
|---|---|
| 10. 55 53 54 52<br>_____ _____ _____ _____ | 11. 77 80 79 78<br>_____ _____ _____ _____ |

12. 70 90 100 80 _____ _____ _____ _____

## ፕሮብሌም መፍታት

1. እሸቱ ከ45 ብር የሚበልጥ፤ ከ47 ብር ግን የሚያንስ ገንዘብ አለው፡፡
   ምን ያክል ገንዘብ አለው? _______ ብር

2. ከግንዱ ላይ ያሉት ኤሊዎች ውሃ ውስጥ ካሉት በ9 ይበልጣሉ፡፡ በውሃ ውስጥ 13 ኤሊዎች አሉ፡፡ ከግንዱ ላይ ስንት ኤሊዎች አሉ? ________ ኤሊዎች

**ሒሳብን በቤት:** ሁለት ባለሁለት ሆሄ ቁጥር በወረቀት ላይ ይጻፉ፡፡ ልጆችዎ ከተጻፉት ቁጥሮች በፊት እና በኋላ የሚገኙትን ቁጥሮች እንዲናገሩ እና እንዲጽፉ ያድርጉ፡፡ እንዲሁም በሁለቱ ቁጥሮች መካከል ላይ የሚሆነው ቁጥር ማን እንደሆነ ይጠይቁ፡፡

## የጨዋታ ጊዜ



እስከ 100 መቁጠር



መነሻ

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 |
| 11 | 12 | 13 | 14 | 15 | 16 | 17 | 18 | 19 | 20 |
| 21 | 22 | 23 | 24 | 25 | 26 | 27 | 28 | 29 | 30 |
| 31 | 32 | 33 | 34 | 35 | 36 | 37 | 38 | 39 | 40 |
| 41 | 42 | 43 | 44 | 45 | 46 | 47 | 48 | 49 | 50 |
